በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

ከ2008-2012 ዓ.ም ሚዛናዊ የስራ አመራር ውጤት ምዘና ስርዓት

(BSC) የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ

(ረቂቅ ሰነድ)

ነሐሴ/ 2007 ዓ.ም
አዲስ አበባ

አጠቃላይ መግቢያ

1. መግቢያ

ትምህርት ዜጎችን በእውቀት፤በአስተሳሰብና በክህሎት በማነጽ ለሀገር ምጣኔ ሀብታዊ፣ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ቴክኖሎጂያዊ ዘላቂ ልማትና ዕድገት በማምጣትና ለህብረተሰቡ ሁለንተናዊ ዕድገት ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ ስለዚህም በትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲያችን አመክንዮአዊ ፣ ለእውነት የሚቆሙ፣ኃላፊነት የሚሰማቸው፣ ለዜጎች ሰብአዊና ፖለቲካዊ መብቶች መረጋገጥ ዘብ የሚቆሙ ዜጎችን በመፍጠር ማህበራዊ ሽግግር ለማረጋገጥ እየሰራ ይገኛል፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ድህነትን በመቀነስና በማስወገድ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት በማስመዝገብ በ2012 ዓ.ም ኢትዮጵያ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ዲሞክራሲያዊ አገሮች ተርታ እንድትሰለፍ ራዕይ አስቀምጦ ለተግባራዊነቱ እየተጋ ነው፡፡

የትምህርት ዘርፍ ልማት ይህንን ሀገራዊ ራዕይ እውን ለማድረግ የሚያስችል አቅም ለመገንባት በርካታ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል፡፡በተልእኮውም ሥራ ፈጣሪ፣ ተወዳዳሪ፣ ለሀገር ሉአላዊነት ዘብ የሚቆሙ፣ ለሀገራዊ ዕሴቶችና ባህል መዳበር የሚተጉ እንዲሁም የሕዝብና የሀገር ፍቅር ያላቸው ዜጎች ለማፍራት እየሠራ ይገኛል፡፡በተጨማሪም ለትምህርት ጥራት መረጋገጥ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፓኬጅን የተገበረ ይገኛል፡፡ ይህ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፓኬጅ በተቀመጠለት የአፈጻጸም አግባብና ደረጃ ተግባራዊ እንዲሆን በዘርፉ መልካም አስተዳደር ማስፈን፣ ተግባራትን በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት መሠረት ማከናወን እንዲሁም ውጤቱን በሚዛናዊ የሥራ አመራርና ውጤት ምዘና ሥርዓት መሠረት መለካትና የተጠያቂነት ሥርዓትን ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡የትምህርት ዘርፉ ተልእኮውን ለመወጣት የተደራጀና ጠንካራ የትምህርት ልማት ሠራዊትን መገንባት፣ የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትንና ድርጊቶችን መታገል፣ የሃይማኖት አክራሪነትን ማስወገድና የልማታዊ ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብን የበላይነት ማረጋገጥ ወሳኝ ነው፡፡

በእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመኑ የትምህርት ዘርፍ ከኪራይ ሰብሳቢነት ለማጽዳት፣መልካም አስተዳደር ለማረጋገጥ፣ የልማታዊና ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብ የበላይነት ለማስፈንና ተግባራትን በጠንካራ የሥራዊት መንፈስ ለመፈጸም የሚያስችል የአመራር ምህዳር ለመፍጠር ተችሏል፡፡በተጨማሪም የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፓኬጅን በመተግበር የትምህርት ጥራት፣ ፍትሐዊነትና ተደራሽነትን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህም በልማት፣ በዲሞክራሲና በመልካም አስተዳደር ግንባታ አዎንታዊ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ ዜጐችን ማፍራት የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፍጠር ተችሏል፡፡ የዕቅዱን ዓላማ ለማሳካትም ሁለት መሠረታዊ አቅጣጫዎች (Strategic Pillars) ተቀምጠው ነበር፡፡

በዕቅዱ የተቀመጠው የመጀመሪያው አቅጣጫ ውጤታማ የትምህርት አገልግሎት መስጠት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የማስፈጸም አቅም ግንባታን ማሳደግ ነበር፡፡ የትምህርትን ተደራሽነትን፣ ብቃትንና ፍትሐዊነትን በማሳደግ ውጤታማ የትምህርት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ በርካታ ፍሬያማ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ ይሁን እንጂ በቅድመ መደበኛና በሁለተኛ ደረጃ፣ በልዩ ፍላጎት ትምህርትና በተግባር ተኮር ጐልማሶች ትምህርት የተከናወኑት ተግባራት ውስንነት እንደነበረባቸው ለመገምገም ተችሏል፡፡ ስለዚህም ይህ ክፍተት በቀጣይ አምስት አመት የእቅድ ዘመን በልዩ ትኩረት ሊሠራበት ይገባል፡፡

የማስፈፀም አቅም ግንባታን በተመለከተ ከቢሮ እስከ ትምህርት ቤት ባለው መዋቅር የሚገኘው አመራርና ፈጻሚ አቅምን ለማሳደግ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ በተለይም በትምህርት ኮማንድ ፖስት አደረጃጀት ከላይ እስከ ታች ያለው አመራር ሦስቱን የትምህርት ልማት ሰራዊት ክንፎች በተቀናጀና በተደራጀ መንገድ በመምራቱ አበረታች ለውጦች ተመዝግበዋል፡፡ በዕቅድ ዘመኑ በአመራሩ፣በፈጻሚው እንዲሁም በመምህራን ላይ የሚታዩ የአመለካከትና የክህሎት ችግሮችን መሠረት ያደረጉ የአቅም ግንባታ መድረኮች በመዘጋጀታቸው በየጊዜው እየተሻሻለ የሚሄድ የአመለካከትና የእውቀት ለውጥ ታይቷል፡፡ አሁንም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመምህራን ላይ ትኩረት በማድረግ የማስፈጸም አቅም ግንባታ ተግባራት ማከናወን ይጠበቅብናል፡፡
ይህ የባላንስድ ስኮር ካርድ ስትራቴጂክ ዕቅድ ዘጠኙን የስኮር ካርድ የግንባታ እና የትግበራ ደረጃዎችን ይዟል፡፡

ከዘጠኙ ደረጃዎች በተጨማሪ የትምህርት ዘርፉ ራዕይ፣ተልዕኮ፣ ተግባር፣ ኃላፊነትና የባለ ድርሻ አካላት ትንተና ተካቷል፡፡በዚህም ሁኔታ የቀጣይ አመስት ዓመት (2008-2012) ስትራቴጂካዊ ዕቅድ ለማሳካት የሚያስችል የጥናት ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡

2. የእቅድ ስትራቴጂክ ዓላማ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮችን መነሻ በማድረግ በስሩ የሚገኙትን የትምህርት ተቋማት እና ግለሰብ ለመምራትና የአፈጻጸማቸውን ውጤት ለመለካት የሚያስችል ሚዛናዊ የሆነ የስራ አመራርና ውጤት ምዘና ስርአት ለመዘርጋት ነው፡፡

3. የስትራቴጂክ እቅዱ አስፈላጊነት

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የትምህርት ፖሊሲያችን ዋንኛ ማጠንጠኛ የሆኑትን የትምህርት ሽፋን፣ ተደራሽነት፤ ፍትሃዊነት፤ ጥራትና ብቃት በማረጋገጥ ለሀገራችን ህዳሴ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ በእውቀት የበለጸጉ፤ በክህሎት የዳበሩና በስነ-ምግባር የታነጹ ዜጎችን ለማፍራት ባለፉት አምስት አመታት ያዘጋጀውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በከፍተኛ ርብርብ ሲተገብር ቆይቷል፡፡ በመሆኑም በትምህርት ሽፋን፤ተደራሽነት፣ፍትሃዊነት እና ጥራት የሚታዩ ችግሮችን በመቅረፍ ለህብረተሰቡ ተገቢውን ምላሽ መስጠት ተችሏል፡፡ ሆኖም ግን የትምህርት ጥራትና ብቃት ከማረጋገጥ አኳያ ውስንነት ይታያል፡፡ ይህን ችግር ለመቅረፍ በአሁኑ ወቅት በሀገራችን እየተመዘገበ ያለውን ልማት ቀጣይነት ለማረጋገጥ፤ በተለይም የትምህርት ልማት ግቦችን በለውጥ መሳሪያዎች (BPR & BSC) በተደራጀ የትምህርት ልማት ሰራዊት በመታገዝ ለመተግበር ያስችል ዘንድ ይህ የቀጣይ አምስት አመታት(2008-2012ዓ.ም) ስትራቴጂክ ስኮር ካርድ እቅድ ከቢሮ እስከ ትምህርት ቤቶች በተዋረድ በማቀድ (Cascading) የትምህርት ውጤታማነት ለማረጋገጥ ነው፡፡

4.የስትራቴጂክ እቅድ ወሰን

የዚህ የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ /BSC/ ዕቅድ ወሰን በቢሮ፣ በክፍለ ከተማና በወረዳ የሚገኙ ዋና ፣ንዑስ ፣ደጋፊ የስራ ሂደቶችን፣ ኬዝ ቲምን፣ የስራ ክፍሎችን፣ ትምህርት ቤቶችን እንዲሁም በስራቸው የሚገኙ ባለሙያዎችን ያጠቃልላል፡፡

5. የሚጠበቅ ውጤቶች

በትምህርት ሴክተሩ በሚዛናዊ የስራ አመራርና ውጤት ምዘና ስርአት በ/BSC/ ማዕቀፍ መሠረት ከላይ እስከ ታች በተገቢው መልኩ ካስኬድ ለማድረግ የሚያስችል የጥናት ሠነድ በተቀመጠው የጊዜ ሠሌዳ በጥራት አዘጋጅቶ ማቅረብ ነው፡፡

6.የጥናቱ ዘዴ

ጥናቱ በየደረጃው ዋና ግብአት አድርጎ የተጠቀመው ቀደም ሲል የተሰራውን የትምህርት ቢሮውን የሁለተኛ ዙር የዕድገትና ትራንስፎርሜን ስትራቴጂክ እቅድ ፣የምዘና ውጤት ትንተና ሰነዶችን ፣አዋጆችን ፣ደንቦችን፣ መመሪያዎችን፣ በትምህርት ዙሪያ የተጠኑ የጥናት ሰነዶችን ማለትም በተለያዩ ጊዜያት በፌዴራል መንግስትና በከተማ አስተዳደሩ የተዘጋጁ ሰነዶችን /የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ፣ የአጠቃላይ ትምህርት ፓኬጅ፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን እንደግብአት በመውሰድ ነው፡፡

ክፍል አንድ

የስትራቴጅና የባላንስድ ስኮር ካርድ ግንባታ ደረጃ፡-

1. ደረጃ አንድ፤- ተቋማዊ ዳሰሳ ማከናወን

ትምህርት ለሀገር ሁለንተናዊ ልማት ወሳኝ መሣሪያ ነው።ትምህርት ልማትን ለማፋጠንና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመገንባት የሚጫወተው ሚና ወሳኝና የማይተካ ነው። በ1986 ዓ.ም. በወጣው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ሪፐብሊክ መንግስትም የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ላይ ዜጎች ችግር ፈቺ፣ ተመራማሪና ሥራ ፈጣሪ በመኾን ለሀገሪቱ አጠቃላይ ዕድገት አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ የሚያስችል ሥርዓት እንደሚፈጠር በግልጽ ተቀምጧል። በዚህ ክፍል የትምህርት ቢሮ ስልጣንና ሀላፊነት፣ውስጣዊና ውጫዊ ትንተና፣ ቁልፍ ችግሮችና የመፍትሔ ሀሳቦች፣አስቻይ ሁኔታዎችና የመጠቀሚያ ዘዴዎች፣ስትራቴጅክ የትኩረት መስክ፣እይታዎች እና የተቋሙ ራዕይ ተልዕኮና እሴቶች በዝርዝር የቀረበበት ክፍል ነው።

1.1 የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የስልጣንና ሃላፊነት ትንተና (Mandate Analysis)

- የከተማዋን ተጨባጭ ሁኔታ በማገናዘብ በሁሉም የትምህርት አይነቶች የመጀመሪያ ደረጃ ሥርዓተ ትምህርት ያዘጋጃል፤የመማሪያ ማስተማሪያ መጽሐፍትና የመምህሩ መምሪያን ያሻሽላል፤መጽሐፍት ያሠራጫል፤ እንዲሁም የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በሁሉም የትምህርት እርከን እንዲሟሉ ያደርጋል፤ተግባራዊነቱንም ይቆጣጠራል።
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር ለሚገኙ የ10ኛ እና 12ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሰጡ ብሔራዊ ፈተናዎችን ያስፈጽማል፤እንዲሁም የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና በማዘጋጀት ተማሪዎችን ያስፈትናል፤እርማቱንም በማካሔድ የማለፊያ ነጥቡን ይወስናል፤ በተጨማሪም በመጀመሪያ ደረጃ /ከ5ኛ - 7ኛ/ እና በ2ኛ ደረጃ /9ኛና 11ኛ ክፍል/ ትምህርት ቤቶች ለሚሰጡ የክፍል ፈተናዎች የማለፊያ ነጥቦችን ይወስናል፤የምስክር ወረቀቶቻቸውንም ብቃት የሚወስን ደረጃ ያዘጋጃል፤ሲፀድቅም በተግባር ላይ መዋሉን ያረጋግጣል።

- በመገናኛ ዘዴዎች የተደገፈ የትምህርት ፕሮግራሞችን ማለትም በመጀመሪያ ደረጃ የሚሰጡ የሬድዮ ትምህርት ፕሮግራሞች በማዘጋጀት በአጋዥ ማስተማሪያነት እንዲሰራጩ ያደርጋል፤ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የፕላዝማ ቴሌቪዥን በማቅረብ ፕሮግራሙን በቅርብ በመከታተል ያስፈጽማል፡፡ ለፕሮግራሞቹ መሳካት የባለሙያ ድጋፍ በመስጠት ለተግባራዊነቱም ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

- የመምህራንና የትምህርት ባለሙያዎችን ብቃታቸውን ለማሳደግ የሚያግዙና ክፍተትን የሚሞሉ ልዩ ልዩ ስልጠናዎችንና የትምህርት ደረጃቸውን የሚያሳድጉበት የትምህርት እድል ይሰጣል፤በሌሎች ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እንዲሰለጥኑ ማድረግ ፣ ክትትልና ድጋፍም ያደርጋል፡፡

- ልዩ የትምህርት ድጋፍ ለሴቶች'ለሕፃናት፣ለጎልማሶችና የልዩ ትምህርት ፍላጎት ላላቸው ዜጎች እንዲሰጥ በማድረግ ፍትሐዊ የትምህርት አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

- በከተማዋ የሚገነቡ አዳዲስና የነባር ትምህርት ቤት ማስፋፋት ግንባታ ስታንዳርዳቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ያደርጋል፤በየደረጃው ተገቢውን የትምህርት ስታንዳርድ ላሟሉ የትምህርት ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፣በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፡፡

- ከከኮተቤ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ጋር በትስስር ይሰራል፡፡በዚህም የቅድመ ስራና የስራ ላይ ስልጠና እንዲሰጥ ያደርጋል፤

- ከዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ የሚመረቁ ሠልጣኝ መምህራንን በመቀበል ለክፍለ ከተሞች ይድልድል፤እንዲሁም ኮሌጁ ደረጃውን የጠበቀ ትምህርት እንዲሰጥ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፡፡

1.2. የተቋሙ ተገልጋዮችና ባለድርሻ አካላት የሚፈልጉትና በቀጣይ የሚጠብቁት /Need and Expectations/

1.2.1 የውስጥ ተገልጋይ ትንተና

ተ.ቁ	ተገልጋይ	ፍላጎት /Needs/	በቀጣይ የሚጠብቋቸው /Expectaions/
1	ተማሪ	• ለሙያው ብቁ የሆኑና በስነ-ምግባር የታነፁ መምህራንና ር/መምህራንን ማፍራት • በትምህርት ቤት ውስጥ መብታቸው ተከብሮ መማር እንዲችሉ ማድረግ • የትምህርት ብክነት ተወግዶ ማየት • በትምህርት ቤት አደረጃጀት ተሳታፊ መሆንና ተሰሚነትን ማግኘት • ዕውቅና ባለው የትምህርት ተቋም መማር • በተግባር የተደገፈ ትምህርት ማግኘት • ምቹና ከአዋኪ ነገሮች የፀዳ የትምህርት ቤት አካባቢ ማግኘት • ጥራቱ የተጠበቀ መጽሐፍት አንድ ለአንድ ማግኘት • በጥራት የሚሰማ የሬድዮና የፕላዝማ ትምህርት ሥርጭት ማሰራጨት • የመማር ማስተማር ሂደቱ ሁሉንም ተማሪዎች እንዲያሳትፍ ማድረግ • ፍትሀዊ የምዘና ስርዓትን ማስፈን • በመረጡት የትምህርት መስክ እንደየዝንባሌያቸው መማር • በቅርብ ርቀት በአካባቢያቸው የመማር ዕድል ማግኘ	• ወደ ከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ተቋማት የሚያሰገባ ውጤት ማምጣት • ብቁ ተወዳዳሪ ውጤታማና ስራ ፈጣሪ ዜጋ መሆን • ለሀገር ገንቢ የሆነ ሚና መጫወት የሚችል ዜጋ መሆን • ወቅታዊና በቴክኖሎጂ የተደገፉ ዕውቀትና ክህሎት ማግኘት • በየትምህርት ዘመኑ መጨረሻ በጥሩ ውጤት ወደ ቀጣዩ ክፍል መዘዋወር

ተ.ቁ	ተገልጋይ	ፍላጎት /Needs/	በቀጣይ የሚጠብቋቸው /Expectaions/
2	ወላጆች	• ልጆቻቸው ደህንነቱ በተረጋገጠ የትምህርት ተቋም በሰላም ተምረው እንዲመለሱ ማድረግ • ለሙያው ብቁ የሆኑና በስነ- ምግባር የታነፁ መምህራንና ር/መምህራንን ማግኘት • በትምህርት ቤት አመራር ማሳተፍን • የትምህርት ተቋማት በተማሪዎች ባህሪ ላይ ተግተው እንዲሰሩ ማድረግ • በወቅቱ ሊሸፈን የሚችል አሳታፊና ከተማሪው ችሎታ ጋራ የተገናዘበ ትምህርት መስጠት • የትምህርት አሰጣጡ በቴክኖሎጂ የታገዘ እንዲሆን ማድረግ • ጥራት ያለው መጽሐፍ ለልጆቻቸው አንድ ለአንድ እንዲዳረስ ማድረግ • በትምህርት አመቱ የተቀመጠውን ትምህርት በአግባቡ ማጠናቀቅ	• ሀገር ተረካቢ፣ በመልካም ስነ- ምግባር የታነፀና በምክንያት የሚያምን ትውልድ /ዜጋን ማፍራት • ልጆቻቸው በዕውቀት በክህሎትና በአመለካከት የተካኑ እንዲሆኑ ማድረግ • ወደ ስራ መስክ ሊያሰማራ የሚችል ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ ትምህርት ልጆቻቸው እንዲያገኙ ማድረግ • የሀገራቸውን ባህልና እሴቶችን ጠንቅቀው እንዲያውቁ ማድረግ • ተወዳዳሪና ስራ ፈጣሪ ዜጋ እንዲሆኑ ማድረግ • ልጆቻቸው ደረጃውን በጠበቀ የትምህርት ተቋም እንዲማሩ ማድረግ
3	ህብረተሰብ	• የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲው ተግባራዊ እንዲሆን • ደረጃውን የጠበቀ የትምህርት አገልግሎት • ተማሪዎች ብቃት ባላቸው መምህራን እንዲማሩ • የትምህርት ተቋማት ሙሉ ሃላፊነት ከተጠያቂነት ጋር ተሰጥቶ	

ተ.ቁ	ተግልጋይ	ፍላጎት /Needs/	በቀጣይ የሚጠብቋቸው /Expectaions/
		ሲተገበር ማየት • መምህራንና ር/መምህራን እንዲሁም ተማሪዎች መብትና ግዴታቸውን የሚረዱበት ሃላፊነትና ተጠያቂነት ያለው አሰራር በትምህርት ተቋማት ሰፍኖ ሲተገበር ማየት • ተማሪዎች ወደ ከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ተቋማትና ወደ ስራ መስክ ሊያሰማራ የሚችል ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ ትምህርት እንዲያገኙ ይሻሉ፡፡ • ወቅታዊና ተገቢ መረጃ ማግኘት	• ለሐገር ልማት ግንባር ቀደም ሚና የሚጫወት ትውልድ ማፍራት • በትምህርት ተቋማት ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምር ማካሔድ • ለህብረተሰቡ ማህበራዊ አገልግሎት የሚሰጡ ተማሪዎች ማፍራት

ተ.ቁ	ተግልጋይ	ፍላጎት /Needs/	በቀጣይ የሚጠብቋቸው /Expectaions/
5	የትምህርት ተቋማት	• በአጭር ጊዜ እውቅና ማግኘትን • የትምህርት ስታንደርድን • ሙያዊ ድጋፍን ይፈልጋሉ • ግብዓት ለሁሉም እንዲዳርስ ማድረግ • ፍትሐዊነት ያለው አስተዳደር/አመራር እንዲኖር ማድረግ • ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃ እንደኖር ማድረግ • ተግባራዊ የማስተማር ልምምድ / practicum/ በቅንጅት መስራት	• በአጭር ጊዜ የተቀላጠፈ አገልግሎትን መስጠት • በስታንደርዱ መሰረት ማስተማር • ውጤታማ መሆንን • የጥሩ ስነ-ምግባር ማዕከላት ማስፋፋት

1.2.2 የባለድርሻ አካላት ትንተና

ተ.ቁ	ባለድርሻ አካላት	ፍላጎት	በቀጣይ የሚፈልጉት
1	የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት	➢ ለዜጋው ጥራቱ የተጠበቀ ትምህርት እንዲደርስ ማድረግ ➢ የትምህርት ብክነት እንዲወገድ ማድረግ ➢ ወደሚቀጥለው የትምህርት ደረጃ ተገቢውን ስብዕናና አመለካከት በማዳበር በጥሩ ውጤት የሚያልፉ ተማሪዎችን ማፍራት	➢ ኃላፊነትን መሸከም የሚችል ዜጋ ማፍራት ➢ ችግር ፈቺና ሥራ ፈጣሪ ትውልድ
2	የአቅም ግንባታ ቢሮ	➢ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም በተሟላ መልኩ እንዲተገበር ማድረግ ➢ የሰው ኃይልና የስልጠና ፍላጎት መረጃ ማሰባሰብ	➢ በሰው ኃይል፤ በአደረጃጀትና በአሰራር አቅሙ የተገነባ ተቋም መፍጠር ➢ የተሰጡ ስልጠናዎች ውጤታማ መሆናቸውን መከታተል ➢ የህብረተሰቡን ፍላጎት ሊያሟላ የሚችል ተቋማት መፍጠር ➢ አገልግሎት የሚሰጥ ተቋምን ማፍራት
3	የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ	➢ የፋይናንስ አሰራርን የተከተለ የበጀት አጠቃቀም መጠቀም ➢ ተፈላጊው ገቢ በህጋዊ ደረሰኝ በወቅቱ ገቢ እንዲደረግ ማድረግ ➢ በጀትን በጥራት ማዘጋጀትና በወቅቱ ማቅረብ	➢ በፋይናንስ አጠቃቀም ብክነት እንዳይኖርና ለውጤታማ ስራ ጥቅም ላይ ማዋልና ሪፖርት ማድረግ

4	ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ	➢ በትምህርት ሴክተሩ ያሉትን ወጣቶች በስፖርታዊ ውድድር እንዲሳተፉ የሴክተሩን ትብብር መጠየቅ	➢ በአካል የጠነከረና በአእምሮ የዳበረ ጤናማ ዜጋን ማፍራት
5	ጤና ቢሮ	➢ የመሰረታዊ ጤና ትምህርት ለመስጠት ሁኔታዎች እንዲመቻችላቸው ፍላጐት ማቅረብ ➢ የስነ ተዋልዶ ጤና እና ፀረ ኤች አይ ቪ ኤድስ ትምህርት በክበባት በኩል እንዲሰጡ ማድረግ	➢ በመሰረተ ጤና ግንዛቤ ያለው ተማሪና የተቋሙን ማህበረሰብ መፍጠር
6	ባህልና ቱሪዝም ቢሮ	➢ ተማሪዎች የክተማውን ታሪካዊና ባህላዊ ገፅታዎች አውቀው ቅርሶችን በመጠበቅ አስተዋጽኦ ማድረግ	➢ የክተማዋን ገፅታዎች የሚያስተዋውቁ' ባህልንና ቅርሶችን የሚጠብቁ ተማሪዎችን ማፍራት
7	ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ	➢ ለሴቶችና ለህፃናት ተገቢውን ድጋፍ የሚያደርጉ የትምህርት ተቋማት መፍጠር	➢ ለሴቶችና ህጻናት የተመቸ የትምህርት ተቋምን መፍጠር ➢ በትምህርታቸው ብቃት ያላቸው ሴቶችን ማፍራት
8	ጥቃቅንና አነስተኛ ኤጀንሲ	➢ ተደራሽ ትምህርት እንዲሰጥ ይፈልጋሉ	➢ ስራ ፈጣሪና ተወዳዳሪ ዜጋን ማፍራት ➢ ለስራ ክቡርነት ዋጋ የሚሰጥ ተማሪ ማፍራት

9	ትምህርት ሚኒስቴር	➢ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲን ተግባራዊ ማድረግ ➢ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅን መተግበር ➢ አስተማማኝ መረጃዎችን በወቅቱ ማቅረብ ➢ ዕድሚያቸው ለትምህርት የደረሱ ሕጻናት ሁሉ ትምህርት ቤት ተመዝግበው መማራቸውን ማረጋገጥ ➢ ለፖሊሲ ማመንጨትና ማሻሻል ግብዓት የሚሆኑ ሃሳቦችን ማቅረብ	➢ የትምህርት ጥራትን ማረጋገጥ ➢ ትምህርት ለሁሉም ዜጋ በፍትሃዊነት ማዳረስ ➢ ብቁ' ተወዳዳሪ' ውጤታማና ስራ ፈጣሪ ዜጋ ማፍራት ➢ ለሀገር ልማት ቁልፍ ሚና መጫወትየሚችል ዜጋ ማፍራት
10	የግል ባለሐብቶች	➢ በስታንዳርዱ መሠረት ተከታታይነት ያለው ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ ➢ ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት	➢ በትምህርት ሥራ ላይ ቴክኒካዊና ሙያዊ ድጋፍ በተግባር መስጠት ➢ ግልጽነትና አሳታፊነት ያለው አሠራር ማጐልበት
11	መያዶች	➢ ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት ➢ ግልጽና ሊያሠሩ የሚችሉ ደንቦችና መመሪያዎች ማዘጋጀት ➢ ሙያዊና ቴክኒካዊ ድጋፍ መስጠት ➢ በጥናት ላይ የተመረኮዙ ፕሮጀክቶችን በወቅቱ ተዘጋጅቶ ማቅረብ ➢ የፋይናንስ ድጋፍን በአግባቡ አሟጦ መጠቀምና በወቅቱ ማወራረድን	➢ ግልጽነትና አሳታፊነት ያለው አሠራር ማጐልበት ➢ ቀልጣፋ የሆነ መልካም ግንኙነትና ቅንጅታዊ አሰራር በመፍጠር የትምህርት ጥራት ማረጋገጥ ➢ የፕሮጀክት አፈጻጸም ሪፖርት ማዘጋጀት

12	የኤች አይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት	➢ በኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ዙሪያ በመስራት በሽታውን መከላከል ➢ የፀረ-ኤችአይቪ/ኤድስ ክበብ እንዲጠናከር ማድረግ	➢ ተማሪዎች፣ የትምህርት ባለሙያዎች አመራሩና ሠራተኞች ራሳቸውን ከኤች አይቪ ኤድስ እንዲጠብቁ የምክር አገልግሎት መስጠት
13	የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን	➢ ተማሪዎች ፣የትምህርት ባለሙያዎችና ሠራተኞች በአካባቢ እንክብካቤ ዙሪያ ግንዛቤ እንዲኖራቸው	➢ አካባቢን ከብክለት የሚጠብቁ ዜጎች
14	የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን	➢ ተማሪዎች በሰላም ውለው እንዲገቡ ተቀናጅተው መስራትን ➢ ተማሪዎች በትራፊክ አደጋ መከላከል ዙሪያ እንዲሳተፉ ድጋፍ መስጠት	➢ ፀጥታውና ደህንነቱ የተጠበቀ የትምህርት አካባቢን መፍጠር
15	የመምህራን ማህበር	➢ የመምህራን የደረጃ ዕድገትና ጥቅማ ጥቅሞች በወቅቱና በፍትሀዊነት መፈፀሙን ማወቅ ➢ ጥራቱ የተጠበቀ ትምህርት ለዜጎች እንዲደርስ ጥረት ማድረግ	➢ የመምህርነት ሙያና የመምህራን መብት መከበርን ማረጋገጥ ➢ ለሀገር ግንባታ አስተዋፅየ ማድረግ የሚችሉ ዜጎችን ማፍራት
16	የስነ- ምግባርና የፀረ- ሙስና ኮሚሽን	➢ የሥነ ዜጋና ሥነ-ምግባር ትምህርት በተጠናከረ ሁኔታ እንዲሰጥ ማድረግ ➢ የሥነ ዜጋና ሥነ-ምግባር ክበብ እንዲጠናከር የግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠት	➢ በስነምግባር የታነፀ፤ ሙስናን የሚፀየፍና የሚዋጋ ዜጋን ማፍራት
17	የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ	➢ በእውቀት፣በክህሎት፣በአመለካከትና በስነ-ምግባር የዳበረ ተማሪን ማፍራት ➢ ወቅታዊና ተገቢ መረጃን ማደራጀት	➢ በሚሠጠው ትምህርት ተማሪዎችን ለሙያ የሚያበቃ ሥርዓተ ትምህርት ማካተት

18	ቀይ መስቀል	➢ በቀይ መስቀል ዓላማ ዙሪያ ግንዛቤን ማሳደግ ➢ ተማሪዎችና የትምህርት ባለሙያዎች በደም ልገሳ ፕሮግራም ላይ በፈቃደኝነት ማሳተፍ ➢ የቀይ መስቀል ክበብ እንዲጠናከር እገዛ ማድረግ	➢ ተማሪዎች የቀይ መስቀል ዓላማ ተረድተው በሰብአዊነትና ርህራሔ አስተሳሰብ መላበስ
24	የአዲስ አበባ ከተማ ሥራ/ አስኪያጅ ጽ/ቤት	➢ በግንባታ ዙሪያ ወቅታዊና ተገቢ መረጃ ማሰባሰብ	➢ ለትምህርት ተቋማት በተዘጋጀው ቦታ ላይ ግንባታዎች በወቅቱ ተገንብተው አገልግሎት ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ ➢ በትምህርት ተቋማት አካባቢ ምቹና የፀዳ ሁኔታ እንዲፈጠር ማድረግ
25	የዲዛይንና ግንባታ አስተዳደር ልማት ቢሮ	➢ በግንባታ ዲዛይን ዙሪያ ወቅታዊና ተገቢ መረጃ መስጠት	➢ የተገነባው ሕንፃ በእንክብካቤ እንዲያዝና ለረጅም ጊዜ አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ
26	የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ	➢ ስለትምህርት ስራ እንቅስቃሴ ተገቢውን መረጃ ማግኘት ➢ የሚኒ ሚዲያ ክበብ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ጥረት ማድረግ	➢ ወቅታዊና ተአማኒነት ያለው መረጃ ➢ ለስነ-ጽሁፍ ዕድገት አስተዋጽኦ የሚያበረክት ዜጋን ማፍራት
27	ሳይንስና ቴክኖሎጂ ቢሮ`	➢ ለሒሳብና ለሳይንስ ትምህርቶች ትኩረት እንዲሰጥ ማድረግ ➢ ቤተ- ሙከራዎች በተሟላ ግብዓት እንዲደራጁ ማድረግ ➢ የሳይንስ ትምህርቶች በተግባር ተደግፈው እንዲሰጡ ማድረግ ➢ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ክበብ ተቋቁሞ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ማድረግ	➢ በሒሳብና ሳይንስ ትምህርቶች ከፍተኛ ዕውቀት፣ክህሎትና አመለካከት እንዲኖር ማድረግ ➢ ለፈጠራ፣ ጥናትና ምርምር ቁልፍ ሚና የሚጫወት ዜጋን ማፍራት

28	የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሮሽን	➢ የዘመኑ ቴክኖሎጂ በፈጠራቸው የኮሙኒኬሽን መሣሪያዎችና ፕሮግራሞች አገልግሎትን መጠቀም መቻል	➢ በመረጃና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም የዳበረ ዜጋ ማፍራት
29	ህግና ፍትህ ጉዳዮች ቢሮ	➢ የህግ የበላይነት እንዲሰፍንና እንዲከበር ማድረግ ➢ የተደራጀና የተሟላ መረጃ ማደራጀት ➢ በህጋዊ መንገድ የተቋቋሙ ተቋማት ማበረታታት	➢ ለህግና ለህገመንግስቱ ተገዥ የሆነ ዜጋ ማፍራት ➢ ወቅታዊና ተአማኒነት ያለው መረጃ ማሰራጨት
30	ንግድና ኢንድስትሪ ቢሮ	➢ ለትምህርት ተቋማት የሙያ ፈቃድና እድሳት አሰጣጥ ላይ በጋራ መስራት ➢ ለተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እንዲሰጣቸው ማድረግ ➢ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርትን በጋራ ማከናወን	➢ በጋራ የመስራት ባህልን ማዳበር ➢ በህግ አግባብ የሚሰሩ ተቋማትን ማፍራት
31	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን	➢ የኤሌክትሪክ ሀይል ፍጆታን በቁጠባ መጠቀም ➢ የኤሌክትሪክ ሀይል ፍጆታ ዋጋ በወቅቱ እንዲከፈል ማድረግ	➢ የኤሌክትሪክ ሀይልን በአግባቡ የሚጠቀም ዜጋ ማፍራት
32	የውሃና ፍሳሽ ባላስልጣን	➢ ውሃን በቁጠባ መጠቀም ➢ ውሃው እንዳይበከል ቅድመ ጥንቃቄ መውሰድ ➢ የውሃ ፍጆታ ዋጋ በወቅቱ እንዲከፈል ማድረግ	➢ ውሃን በአግባቡ የሚጠቀም ዜጋ ማፍራት

1.3 የውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎች ትንተና

1.3.1 የትምህርት ሴክተሩ የውስጣዊ ሁኔታዎች ትንተና

ተ.ቁ.	ውስጣዊ ሁኔታዎች	ጠንካራ ጎኖች/Strength/	ውሱንነት/Limitations/
1	የትምህርት አመራሩ	➢ ግልጽ ራዕይ፣ተልዕኮና ዓላማ መኖሩ ➢ ያልተማከለ አደረጃጀትና አሠራር መዘርጋቱ ➢ የትምህርት ስራን ለማጠናከር የህዝብ ንቅናቄ መፈጠሩ ➢ የክትትልና ድጋፍ አግባብ ተግባራዊ መሆኑ ➢ ህብረተሰቡን በማስተባበር ለተቋማት ገቢ ማስገኘት መቻሉ ➢ ለደረጃው የሚመጥኑ መምህራን፣ ር/መምህራንና የሱፐርቫይዘሮች መመደባቸውና የደረጃ ዕድገት ተጠናክሮ እንዲቀጥል መደረጉ ➢ ለርዕሰ መምህራንና መምህራን የማትጊያ የትምህርት እድልና ለቤት አበል ድጋፍ እንዲያገኙ መደረጉ፣	➢ የከተማዋን ፈጣንና ውስብስብ የልማትና የዕድገት ማዕበል ንቅናቄ የሚጠይቀውን የጠራና ሩቅ አሳቢ አመራር የመስጠት ክፍተት፣መኖር ➢ አቅሙን በሙሉ ለትምህርት ጥራት የሰጠ አመራር አለመጠናከሩ፣ ➢ የለውጥ መሳሪያዎችን (BSC & BPR) በቁርጠኝነት ይዞ ተግባራዊ ያለማድረጉ፣ ➢ በዕቅድ ከመመራት ይልቅ በደራሽ ሥራዎች የመጠመድ ሁኔታ መታየት ➢ በትምህርት አገልግሎት ዘርፉ የህብረተሰቡን ባለቤትነት በሚፈለገው መጠን ማሳተፍ አለመቻል ➢ በየአደረጃጀቱ ቋሚ የሆነ የክትትልና ድጋፍ አግባብን አለማጠናከር ➢ ለአሠራር አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችና መመሪያዎች ሰነዶች በአግባቡ አለመያዝና አለመጠቀም ➢ በትምህርት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ የትምህርት ልማት ዘርፍና የትምህርት ጥራት ፓኬጅ ላይ በቂ ግንዛቤ አለመያዝ ➢ የውሣኔ አሰጣጥ መዘግየት

2	ተቋማዊ አደረጃጀት	➢ የወላጆች፣ ተማሪዎችና መምህራን ህብረት (ወተመህ) አደረጃጀት ከቢሮ እስከ ት/ቤት መቋቋሙ ➢ በሳይንስና ሂሳብ ትምህርቶች ልዩ ትኩረት በመስጠት ከቢሮ እስከ ት/ቤት አደረጃጀት መፈጠሩ ➢ የኮማንድ ፖስት አደረጃጀት መፈጠሩ ➢ የመሰረታዊ የስራ ሂደት ጥናት መከለሱና ስራዎች ከከተማ እስከ ት/ቤት ድረስ መለየታቸው ➢ የጉድኝት ማዕከላት መደራጀታቸውና በክላስተር ሱፐርቫይዘር እንዲመሩ መደረጉ ➢ የትምህርት አገልግሎትን ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል ተገቢ አደረጃጀት መኖሩ ➢ የመምህራንና የፈጻሚዎች 1ለ5 አደረጃጀት መኖሩ	➢ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ1ለ5 አደረጃጀት የግንዛቤና ቨአመለካከት ችግር መኖሩ ➢ የወ.ተ.መ.ህ አደረጃጀት በሁሉም ት/ቤቶች በወጥነት ተግባራዊ አለመሆን ➢ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ሥርዓት አለመዘርጋት፣ ➢ ከላይ እስከ ታች የተቀናጀ አሰራር አለማጠናከርና ተናብቦ አለመሄድ ➢ ሦስቱን አቅሞች አቀናጅቶ የጋራ ዓላማ ለሆነው የትምህርት ጥራት መረጋገጥ እንዲረባረብ አለማድረግ (በሰራዊት አቅም መስራት አለመቻል)
3	የሰው ኃይል	➢ በየደረጃው ባለው መዋቀር የባለሙያዎችን ስብጥርና ብዛትት ለመሟላት የሚደረግ እንቅስቃሴ መኖሩ፣ ➢ በፖሊሲና ስትራቴጂዎች እንዲሁም መመሪያዎች ላይ ግንዛቤው መደረጉ ➢ ከሥራ ሰዓት ውጪ በራስ ተነሳሽነት የመስራት ሁኔታ መሻሻሉ ፣ ➢ በየት/ቤቱ ለደረጃው የሚመጥኑ ርዕሰ መምህራንና መምህራን መሟላታቸው	➢ የከተማዋ ፈጣን የዕድገት ለውጥ በሚጠይቀው ደረጃ ራስን በማብቃት ለሕዝቡ ጥራትና ብቃት ያለው አገልግሎት ለመስጠት ዝግጁነት ማነስ ➢ የውድድር ስሜት የሚፈጥር የማትጊያ ሥርዓት አለመጠናከር፣ ➢ ከጠባቂነት አለመላቀቅ ➢ የህዝብ አገልጋይነት ስሜት አለማዳበር፣

4	ፋይናንስ	➢ በየደረጃው ያልተማከለ የበጀት አመዳደብ መኖሩ፣ ➢ ሕብረተሰቡን፣ አለም አቀፍ ድርጅቶችና መያዶችን በማሳተፍ የፋይናንስ አቅምን ለማሳደግ መቻሉ፣ ➢ በመሰናዶ ትምህርት ቤቶች የወጪ መጋራት ሥርዓት ተግባራዊ መደረጉ፡፡ ➢ ዘመናዊ የበጀት አጠቃቀም የመረጃ መረብ (IBEX) መኖሩ ➢ ት/ቤቶች የውስጥ ገቢያቸውን መጠቀም የሚችሉበትን አሠራር መዘርጋቱ፣	➢ በትምህርት ቤቶች ፍትሀዊ የበጀት ክፍፍልን ተግባራዊ ለማድረግ የአፈጻፀም ችግር መኖሩ ➢ የተፈቀደ በጀትን በወቅቱ መጠቀም አለመቻልና በወቅቱ አለማወራረድ፣ ➢ ቀልጣፋና ጥራት ያለው የግዥ ስርዓትና የንብረት አስተዳደር አለመኖር፣ ➢ ልዩ ልዩ የገቢ ማስገኛ ፕሮጀክቶችን ቀርጾ በሚፈለገው መጠን ሥራ ላይ አለማዋል፤ ➢ በወረዳ ለየዘርፉ የሚመደብ በጀት አነስተኛ መሆን
5	ግብዓት/ቁሳዊ/	➢ ለግል ት/ቤቶች መጻህፍት በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኙ መደረጉ ➢ ፈጣን አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች መጠቀም መቻሉ ➢ ፕላዝማ ቴሌቪዥኖች፣ኮምፒዩተሮችና ኢንተርኔት በአብዛኛው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መሟላቱ ➢ የትምህርት የሬዲዮ ጣቢያ(FM 94.7) መከፈቱ ➢ ትምህርት ቢሮው ሁሉንም አገልግሎት በአንድ አካባቢ መስጠት በሚያስችል ሁኔታ በአዲስ ህንጻ መደራጀቱ	➢ በከተማዋ ገጠራማ አካባቢዎች በቂ ት/ቤቶች አለመገንባት፣ ➢ ግብአትን በአግባቡ አለመጠቀም ➢ በወረዳ ለባለሙያዎች የሚሆን የቢሮና ቁሳቁስ እጥረት መኖሩ

6	የአሰራር ስርአት	➢ የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ የትምህርት ጥራት ፓኬጅ ተግባራዊ መደረጉ፣ ➢ ቢሮው የተለያዩ መመሪያዎችን በማዘጋጀት እስከ ት/ቤቶች ድረስ ማሰራጨትና ማስተዋወቁ ➢ የማታ ትምህርት፣ የጎልማሶች ተግባር ተኮር፣ የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርትና የርቀት ትምህርት አገልግሎት ለነዋሪው መሰጠቱ፣ ➢ ሥርዓተ ትምህርቱን በየወቅቱ በመገምገም የማሻሻል ሥራ መከናወኑ፣ ወጥነት ያለው አተገባበር እንዲኖርም መመሪያ ማሰራጨቱ	➢ ትምህርት የሚያቋርጡና የሚደግሙ ተማሪዎች ብዛት ሙሉ በሙሉ መቀነስ አለመቻል፣ የተማሪዎች ውጤትም በሚፈለገው ደረጃ አለመሻሻል ➢ ለልዩ ፍላጐት ህፃናት የተሟላ አገልግሎት አለመስጠት፣ ➢ ት/ቤቶች ስታንዳርዳቸውን የጠበቁ አለመሆን ➢ በት/ቤቶች የሚካሄድ የመምህራን ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ፕሮግራሞች የቅርብ ድጋፍና ክትትል አለማድረግ፣ ➢ የት/ቤት ማሻሻል ፕሮግራም በተቀመጡት አበይ ርዕሰ ጉዳዮችና ስታንዳርዶች መሠረት በሚፈለገው ደረጃ ተግባራዊ አለመሆኑና የሚፈለገው ውጤት ላይ መድረስ አለመቻሉ፣ ➢ የዘመናዊ መረጃ ቴክኖሎጂን (ICT) በየደረጃው ባሉት የትምህርት እርከኖች መጠቀም አለመቻል፣

7	መልካም አስተዳደርና አገልግሎት አሰጣጥ	➢ ግልጽ የትምህርት ራዕይ መኖሩ፣ ➢ አመራሩ እና ፈጻሚው የህዝብ አገልጋይነት ስሜት እንዲያዳብር የተለያዩ የአመለካከት ለውጥ የሚያመጡ የአቅም መገንቢያ ስልቶች ተግባራዊ እየሆኑ መምጣቱ፣ ➢ ቁልፍ የሆኑ የልማትና የመልካም አስተዳደር ችግሮች ነጥረው መውጣታቸው እና በየደረጃው ካለው አመራር እና ፈጻሚ ጋር የጋራ መግባባት መደረሱ ፣ ➢ በመልካም አስተዳደርና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚታዩ ችግሮችን በአጭር፣ በመካከለኛ እና በረጅም ጊዜ ለመፍታት የተደራጀ ዕቅድ በማውጣት ለመተገበር እየተደረገ ያለው ጥረት አበረታች መሆኑ፣ ➢ ያልተማከለ አስተዳደር ተግባራዊ መሆን መጀመሩ፣ ➢ የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ትግበራ ጥናት ተከልሶ ተግባራዊ ማድረግ መጀመሩ ➢ አገልግሎት አሰጣጡ በዘመናዊ የመረጃ ስርዓት መደገፍ መጀመሩ፣ ➢ የህዝብ ንቅናቄ ስራዎችና የህብረተሰብ ተሳትፎ እየተሻሻለ መምጣቱ፣	➢ ለህዝቡ የመንግስትን ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በሚገባ ከማስገንዘብና በባለቤትነት ስሜት ከመፈፀም አንፃር ውስንነት መኖሩ፣ ➢ የግልጽነትና የተጠያቂነት አሰራር በተሟላ መልኩ አለመተግበሩ፣ ➢ ተቋማት አሰራራቸውን የበለጠ ግልጽና ተጠያቂ አለማድረጋቸውና ይህም ለኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር የተመቸ መሆኑ፣ ➢ ተቋማት ለተገልጋዮቻቸው የሚሰጡት ትኩረት በተጀመረበት ፍጥነት አለመቀጠሉና ወጣ ገባነት የበዛበት መሆኑ፣ ➢ ለተገልጋዩ የሚሰጡ አገልግሎቶች በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት በተሟላ መልኩ ተግባራዊ አለመደረጋቸው፣ ➢ ለህብረተሰቡ የሚሰጡ አገልግሎቶች በታሰበው ፍጥነት እና ውጤታማነት ለህበረተሰቡ አለመሰጠታቸውና የአገልግሎት አሰጣጥና የመልካም አስተዳደር ችግሮች እየተጠራቀሙ መምጣታቸው፣ ➢ አመራሩም ሆነ ፈፃሚው ተገልጋዩን አክብሮና ደንበኛ ንጉስ ነው ብሎ ከማስተናገድ አንፃር ሰፊ ክፍተት መታየቱ፣

1.3.2 የትምህርት ሴክተሩ የውጫ ሁኔታዎች ትተና (PESTE Analysis)

ተቁ	ውጪያዊ ሁኔታዎች	መልካም አጋጣሚዎች /Opportunities/	ስጋቶች /Threats/
1	ፖለቲካዊ	➢ በከተማችን የተጀመረውን ልማት ለማስቀጠል በህዝቡ ዘንድ የተፈጠረዉ ልማታዊ መነሳሳት፣ ➢ የትምህርት ስልጠና ፖሊሲና ስትራቴጂ ፣የፖሊሲ ማስፈጻሚያ የትምህርት ልማት ፕሮግራም፤ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅ ፣ የአዲስ አበባ ከተማ ቻርተርና የአስፈፃሚና የማዘጋጀ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ እና ሌሎች አዋጆች መኖራቸው፣ ➢ አዲስ አበባ የአገሪቷ መዲና የአለም አቀፍ ድርጅቶች መገኛ መሆኗ ለዲፕሎማሲያዊ እድገት መፋጠን አስተዋጽኦ ያለው መሆኑ ፣ ➢ በየደረጃው የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ እየተጠናከረ መሄዱ፣ ➢ ያልተማከለ አሠራርና የመልካም አስተዳደር ሥርዓት መዘርጋቱ፣ ➢ የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም ተጠናክሮ መቀጠሉ፣ ➢ የከተማው አስተዳደር ለትምህርት ዘርፉ ልዩ ትኩረት መስጠቱ፣	➢ የኪራይ ሳብሰቢነት ፖለቲካል ኢኮኖሚ አስተሳሰብና ተግባር የበላይነት ፣ ➢ የመልካም አስተዳደር ችግር ➢ የትምህርት ህግ ፀድቆ ተግባራዊ አለመሆኑ፣ ➢ የሃይማኖት አክራሪነት፣

2	ኢኮኖሚያዊ	➢ ለትምህርት አገልግሎት ዘርፉ የሚመድበው በጀት መጠን እየጨመረ መሄዱ፣ ➢ ከታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ጋር ተያይዞ የትምህርት ማህበረሰብ የቁጠባ ባህል እያደገ መምጣቱ፣ ➢ ተከታታይ የኢኮኖሚ እድገት እየተመዘገበ ያለ መሆኑ፣ ➢ በርካታ የስራ ዕድሎች እየተፈጠሩ መሆናቸው፣ ➢ ኢኮኖሚያዊ መሰረተ ልማቶች መንገድ፣ መብራት፣ ውሃ፣ ቴሌኮሙንኬሽን እየተስፋፉ መሆናቸዉ፣ ➢ ጎብረተሰቡና የልማታዊ ባለሀብቶች በትምህርት አገልግሎት ዘርፉ የሚያደርጉት ተሳትፎና ኢንቨስትመንት ማደጉ፣ ➢ አለም አቀፍ ለጋሾች፣ አበዳሪ ድርጅቶችና መንግሥታት ለትምህርት አገልግሎት ዘርፉ የሚሰጡት ድጋፍ መጨመሩ፤ ➢ የመንግስት ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢያቸውን በቀጥታ መጠቀም የሚችሉበት ሁኔታ መመቻቸቱ	➢ አነስተኛ ገቢ ያላቸው ወላጆች በመኖራቸው በተማሪዎችየትምህርትአቀባበል ላይ አለታዊተፅእኖማሳደሩናየትምህርትብክነትከፍተኛእንዲሆንማድረጉ ➢ የኑሮ ውድነት በዝቅተኛ ገቢ የሕብረተሰብ ክፍል የሚያሳድረው ጫና በሕጻናት የትምህርት ክትትልና አቀባበል ላይ ተጽእኖ ማሳደሩ ➢ የከተማዋ ማስፋፊያ አካባቢዎች ትምህርትን ተደራሽ ከማድረግ አንጻር ጫና ሊፈጥር ይችላል
3	ማህበራዊ	➢ ማህበራዊ መሰረተ ልማቶች እየተስፋፉ መሆናቸው (ትምህርት ቤቶች፣ ጤና ጣቢያ፣ የኤች አይ ቪ ኤድስ የምክር አገልግሎት ማዕከላት፣ወላጆቻቸውንያጡ ህጻናት እንክብካቤ ማዕከላት) ➢ ህብረተሰቡ ለትምህርትና ጤና አጠባበቅ ያለው ግንዛቤ ዕያደገ መምጣቱ ➢ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ተዳራሽ መሆኑ፣ ➢ በHIV/AIDS መከላከልና መቆጣጠር ሥራ ላይና አካል ጉዳተኞችን በሚያግዙ ተግባራት ላይ የተሠማሩ ባለድርሻ አካላት ከትምህርት ቢሮ ጋር ተባብረው መሥራታቸው፣	➢ የመጤ ልማዶችመስፋፋት ፣ ➢ ወላጆች ስለ ልጆቻቸው የትምህርት አቀባበልና ስነ ምግባር የሚደረግ ክትትል፣ ➢ የሕዝብ ፍልሰት፣ ➢ የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናትና ወጣቶች ፣ ➢ በት/ቤቶች አካባቢ አዋኪ ሁኔታዎች ➢ የኤች አይ ቪ/ ኤድስ ➢ ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የሚሰጥ ትኩረት

4	ቴክኖሎጂያዊ	➢ በዘመነ ግሎባላይዜሽን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ትስስር መኖር፣ ➢ የኢንተርኔት አገልግሎት እየተስፋፋ መምጣቱ፣ ➢ ዘመናዊ የትምህርት መረጃና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም መስፋፋት፣ ➢ የቴክኖሎጂ ውጤት የሆኑ የትምህርት ግብዓቶች በሀገር ውስጥ መመረት መጀመራቸው	➢ አመራሩ፣ባለሙያውና መምህራን ቴክኖሎጂን ለመጠቀም ያለው ብቃት ችግር ፣ ➢ የቴክኖሎጂው ግብአት ችግር፣ ➢ ኢኮቴን ለትምህርት አገልግሎት ከመጠቀም ውጪ ለጎጂ ድርጊቶች ማዋል
5	አካባቢያዊ	➢ የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂ መዘጋጀቱ ➢ በአካባቢ ጥበቃ ላይ የሚሰሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መኖራቸው	➢ ለአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ የሚደረገው ጥረት ➢ አገልግሎት የማይሰጡ ኬሚካሎችን አካባቢን በማይጎዳ ሁኔታ ለማስወገድ የእውቀትና ክህሎት ማነስ

1.4 ቁልፍችግሮች (Pains) እናየመፍትሄ ሃሳቦች(Possible Interventions)

ቁልፍ ችግሮች ማለት የውስጥ ድክመትና ውጫዊ ስጋት /ቁልፍ ችግሮች =ድክመት + ስጋት/

ውሕደት ሲሆን በዚህም መሠረት ለእያንዳንዱ ቁልፍ ችግር የመፍትሔ ሀሳቦች ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ ቀርበዋል፡፡

ተ.ቁ	ቁልፍ ችግሮች/Pains/	የመፍትሄ ሀሳቦች/Possible Interventions/
1	የትምህርት ተቋማት የትምህርት ቤት መሻሻል መርሃግብርን ተጠቅመው ወደ ሚፈለገው የጥራት ደረጃ አለመድረስ	➢ ለመማር ማስተማሩ ምቹ አካባቢና ሁኔታ በመፍጠር ➢ ወላጆች በልጆቻቸው ትምህርት ውስጥ የሚያደርጉትን የተሳትፎ ደረጃ ማሳደግ ➢ በህብረተሰቡና በባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ትምህርት ቤቶችን ከአዋኪ ሁኔታዎች የፀዱ ማድረግ ➢ የትምህርት ቤት አመራርና አስተዳደርን በማጠናከር ➢ የመማር ማስተማሩን ሂደት በማጠናከር ➢ በየደረጃው በሚገኙ የትምህርት ተቋማት የተጀመረውን የትምህርት ንቅናቄ ስራ አጠናክሮ በመቀጠል
2	የመምህራንና የትምህርት ባለሙያዎች የአመለካከት፣ የተነሳሽነትና ብቃት በሚፈለገው ደረጃ ላይ አለመገኘቱ	➢ መምህራንና የትምህርት ባለሙያዎችን ማነቃቃት የሚችል ምቹ የስራ አካባቢና ሁኔታ መፍጠር፣ አመራሩን የማብቃት፣ የመደገፍና፣ የመገምገም ስርዓት አጠናክሮ በመቀጠል ➢ መምህራን የመምህርነትን መራሔ ሙያ ጠንቅቀው እንዲያውቁ የሙያ ትውውቅና የተከታታይ ሙያ ማሻሻያ ፕሮግራም አጠናክሮ በመቀጠል ➢ የመምህራን ምልመላና አሰለጣጠን ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን በማድረግ

3	የመማር ማስተማር ሂደቱ በየደረጃው ከተማሪዎች የሚጠበቁ ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ለማስጨበጥና ውጤታማ ተማሪዎችን ማፍራት አለማስቻሉ	➢ ለመምህራንና ለትምህርት ባለሙያዎች ውጤታማ የሆኑና የዘመኑ ቴክኖሎጂ የፈጠራቸውን የማስተማሪያ ሥነ ዘዴዎችና የምዘና ስርዓቶችን የተመለከቱ ስልጠናዎች መስጠት፣ድጋፍና ክትትል በማድረግ ➢ የተከታታይ ምዘናን አጠናክሮ በተግባር ላይ እንዲውል በማድረግ ➢ ደረጃውን የጠበቀ የሥርዓተ ትምህርት ክለሳ በማድረግ ➢ ትምህርት ቤቶችን በአስፈላጊው የትምህርት ግብአት እንዲሟሉ በማድረግ
4	የትምህርት ብቃት ማሳደግ አለመቻል	➢ ምቹ የትምህርት አካባቢና ሁኔታ በመፍጠር ➢ የማስተማር ሥነዘዴን ተማሪ ተኮር በማድረግና ፍትሃዊና ተከታታይ የምዘና ሥርዓት በመጠቀም የሚደግሙና የሚያቋርጡ ተማሪዎችን መቀነስ ➢ የወላጅና የትምህርት ቤት ግንኙነትን ማጠናከር
5	በስነዜጋና ስነምግባር ትምህርት በቂ የሰለጠኑ መምህራን አለመኖር በተማሪዎች፣በመምህራንና በወላጆች ዘንድ ያለው የአመለካከት ችግር በተማሪዎች ላይ የሚጠበቀውን የባህሪ ለውጥ ማምጣት አለመቻል	➢ በትምህርቱ ላይ ለመምህራን ፣ለትምህርት ባለሙያዎችና ለህብረተሰቡ የአመለካከት ለዉጥ ሊያመጣ በሚችል መልኩ ግንዛቤ ማስጨበጥ ➢ የስነ ዜጋና የስነምግባር ትምህርትን በተማሪ ተኮር የማስተማር ስነ ዘዴ በመጠቀም ማስተማርና የስነዜጋና ስነምግባር ክበብ በስፋት ተጠናክሮ እንዲሰራ በማድረግ

		➢ ተማሪዎች የትምህርትን ጠቀሜታ በይበልጥ እንዲረዱ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስርዓት መዘርጋት ➢ ከተማሪ ወላጆች ጋር ግንኙነትን ማጠናከር ➢ በሚፈለገው መጠን በሙያው የሰለጠኑ መምህራን ማፍራት
6	በየደረጃው ያሉ የትምህርት አመራር ብቃት፣ ተነሳሽነትና ተጠያቂነት አናሳ መሆንና የትምህርት ተቋማትንም ውጤታማ ማድረግ አለማስቻሉ	➢ የተሟላ እቅድ በማዘጋጀት ከትምህርት ቢሮ እስከ ትምህርት ቤት ያለው አመራርና ፈፃሚ አካል በትምህርት ልማት ንቅናቄ ውስጥ ገብቶ በባለቤትነት ሊመራ የሚያስችል ስልት መቀየስ ➢ የር/መምህራንና ሱፐርቫይዛሮች ምደባ በመመሪያው መሰረት በመፈጸም ➢ ብቃትና ተነሳሽነትን ማሳደግ የሚያስችል የአመራር ስልጠና መስጠት ➢ ክፍተት ተኮር ስልጠና መስጠትና ስልጠና ያስገኘውን ውጤት በመገምገም ግብረ መልስ በመስጠት ➢ የተጠያቂነት ሥርዓት በማስፈን ➢ በትምህርት ሴክተር ሴቶች በተፈለገው ደረጃ ወደ አመራር እንዲመጡ የማብቃት ስራ በመስራት

7	የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂን በብቃት የመጠቀም ክፍተትና የግብአት አለመሟላት	➢ የዘመኑ ቴክኖሎጂ የፈጠራቸውን መሳሪያዎች አጠቃቀም ብቃት ማሳደግ /የýላዝማ 'የሬድዮ ትምህርት ኮምፒውተርና ኢንተርኔት በብቃት የመጠቀም አቅም ማጎልበት/ ➢ የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሳሪያዎችን ሚሟላት
8	የትምህርት ዕድል ያላገኙ ዜጎች መኖር	➢ የትምህርት ተቋማት ግንባታ በገጠራማ የከተማው አካባቢ ማዳረስ ➢ በከተማዋ የቅድመ መደበኛ ትምህርት አቅርቦትን በማስፋፋት ➢ የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህር አቅርቦትን በማስፋፋት
9	የትምህርት ፍትሀዊነት በሚፈለገው መጠን አለመረጋገጡ	➢ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ላላቸው ዜጎች የትምህርት ዕድል በማዳረስ ➢ ለሴቶች ልዩ ድጋፍ በመስጠት
10	ለትምህርት የሚመደበው ሃብት በአግባቡ ስራ ላይ ውሎ ተፈላጊውን ውጤት ማስገኘት አለመቻሉ/ውጤታማ የበጀት አጠቃቀም ችግር በመኖሩ/	➢ ሀብትን በአግባቡ በመጠቀምና የፋይናንስ አሰራርን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በማስደገፍ ስልጠና በመስጠት' ድጋፍና ክትትል በማድረግ' ህብረተሰቡንና መያዶችን በማሳተፍ' ገቢን ማሳደግና የትምህርት ግብአትማሟላት
11	የትምህርትን ስራ ለማጎልበት የተጠናከረ ቅንጅታዊ አሰራር አለመኖር ፤ወጥ የመረጃና የተግባቦት ስርዓት አለመጎልበት	➢ የትምህርት ስራን ለማጎልበት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ ወጥ የሆነ የመረጃ አያያዝና የተግባቦት ስርዓት መዘርጋትና ስልጠና በመስጠት
12	የመማር ማስተማር ስራን በጥናትና ምርምር አለማጎልበት	➢ ጥናትና ምርምርን የመማርና ማስተማር ሂደትን ችግር በሚፈታ መልኩ ማካሄድ' አደረጃጀቱንም ከቢሮ እስከ ትምህርት ተቋማት ማጠናከር'ድጋፍና ክትትል በማድረግ

1.5 አስቻይሁኔታዎች/Enablers/ እና የመጠቀሚያዘዴዎች/ Measures to Exploit/

አስቻይ ሁኔታ ማለት የውስጥ ጥንካሬና የውጫዊ መልካም አጋጣሚ /አስቻይ ሁኔታ= ጥንካሬ + መልካም አጋጣሚ/ ውሕደት ሲሆን ለእያንዳንዱ አስቻይ ሁኔታም የመጠቀሚያ ዘዴዎች በሰንጠረዡ ተካተዋል፡፡

ተ.ቁ	አስቻይ ሁኔታዎች/Enablers/	አስቻይ ሁኔታዎችን መጠቀሚያ ዘዴዎች/ Measures to Exploit/
1	የትምህርትናሥልጠናፖሊሲ' ስትራቴጂ'አዋጆች ደንቦችና መመሪያዎች አሰሪ መሆናቸውና የትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅ ትግበራ መጀመሩ	• ለትምህርት ባለሙያዎችና ለባለድርh አካላት የትምህርትና ስልጠና þሊሲ ስትራቴጂን አዋጆችን ደንቦችና መመሪያዎች ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ በመስራት • የትምህርት ጥራት ማረጋጫ ፓኬጅ ላይ ግንዛቤ በመፍጠር በዘላቂነት መልኩ ትግበራውን አጠናክሮ በመቀጠል
2	ለተማሪዎች ለመምህራንና ለትምህርት ባለሙያዎች በተለያዩ የመንግስት ፖሊሲና ስትራቴጂ ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች መሰጠቱና በትምህርት ሴክተሩ የጋራ መግባባት መፈጠሩ	•የሰለጠነውን የሰው ሀይል በአመራርና በተለያዩ ስራዎች በማሳተፍ • የተፈጠረውን ግንዛቤ መሠረት በማድረግ ለመማር ማስተማር ስራ በመጠቀም
3	ያልተማከለ አስተዳደር መኖሩና የትምህርት ስራን ውጤታማ ለማድረግ የህዝብ ንቅናቄ መፈጠር መጀመሩ	• ህብረተሰቡን በትምህርት ስራ ላይ በማሳተፍ የትምህርት ተቋማትን በባለቤትነት እንዲመሩ በማድረግ

ተ.ቁ	አስቻይ ሁኔታዎች/Enablers/	አስቻይ ሁኔታዎችን መጠቀሚያ ዘዴዎች/ Measures to Exploit/
4	መንግስት ለትምህርት በሰጠው ልዩ ትኩረትና የትምህርቱን ስራ የሚደግፉ ሀገራዊና አለምአቀፋዊ ድርጅቶች በመኖራቸው የትምህርት ሴክተሩ አመታዊ በጀት እያደገ መምጣቱ	• የተገኘውን በጀት በአግባቡ በመጠቀምና በትምህርት ስራ ላይ በማዋል
5	የመምህራንና የትምህርት ባለሙያዎችን ብቃት ሊያሳድጉ የሚችሉ ስልጠናዎች ሥርዓት መዘርጋቱና እየተተገበሩ መሆኑ	• መምህራንና የትምህርት ባለሙያዎች ባገኙት ዕውቀትና ክህሎት የመማር ማስተማር ስራን እንዲያነለብቱ በማድረግ • የሰለጠነውን የሰው ሃይል በተለያዩ ስራዎች በማሳተፍ • የወሰዱትን ስልጠና ለሌሎች የሚያካፍለበትን ሁኔታ በማመቻቸት
6	በከተማው የሰለጠነ የሰው ሀይል መኖር እና በትምህርት ሴክተሩ ለየደረጃው የሚያስፈልግ የሰው ሃይል መኖሩ	• የሰለጠነ የሰው ሃይል የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ጎልቶ እንዲወጣ በማድረግ • የሰው ሀይል ክፍተት ሲፈጠር ለማሟላት በመጠቀም
7	በመንግስት ፣በህብረተሰቡ፣ በለጋሽ ድርጅቶች ድጋፍና በግል ባለሀብቶች/የግል ትምህርት ተቋማት አዳዲስ ትምህርት ቤቶች መገንባታቸውና ለዜጎች የትምህርት ዕድል ለማዳረስ ምቹ ሁኔታ መፍጠሩ	• ዜጎችን በተገኘው የትምህርት ዕድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ

ተ.ቁ	አስቻይ ሁኔታዎች/Enablers/	አስቻይ ሁኔታዎችን መጠቀሚያ ዘዴዎች/ Measures to Exploit/
8	መንግስት በሰጠው ልዩ ትኩረትና ህብረተሰቡ የትምህርትን ጠቀሜታ በመረዳቱ የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ እያደገ መምጣቱ	በመንግስትና በህብረተሰቡ በተሰጠው ትኩረት የሴት ተማሪዎችን ተሳትፎና ውጤት ለማሳደግ በመጠቀም
9	የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም ተጠናክሮ በመቀጠሉ የተሻሻለ አገልግሎት መሰጠቱ	• የተፈጠረውን የተሻሻለ አገልግሎት በማጠናከር
10	መምህራንን' ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮችን የሚያበረታታ የማትጊያ ስርዓት መዘርጋቱ	• በውጤት ላይ በመመስረት የተዘረጋውን የማትጊያ ስርዓት በአግባቡ በመጠቀም
11	የትምህርት ስርዓቱ በመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ /ICT/ መደገፉ	• የሰው ሃይል ክህሎትን በማሳደግ • የትምህርት ተቋማትን በመረጃ መረብ በማስተሳሰር
12	በየትምህርት ተቋማቱ ምርጥ ተሞክሮዎችን ለማስፋፋት የተሰጠው ልዩ ትኩረትና የጉድኝት ማዕከላት በአዲስ መልክ መደራጀታቸው	- መልካም ተሞክሮዎችን በመቀመር ለሌሎች ተቋማት በማዳረስ - የጉድኝት ማዕከላትን የስልጠናና ጥናትና ምርምር ማዕከል በማድረግ - በጉድኝት ማዕከላት ያለውን ሀብት በጋራ እንዲጠቀሙ በማድረግ
13	የተቀናጀ የኤች አይቪ/ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ስርዓት መዘርጋት	ኤች አይቪ/ ኤድስ ሚይንስትሪም በማድረግ'የአቻ ለአቻ'የሕይወት ክህሎት ትምህርትና የፀረ ኤች አይቪ ኤድስ ክበባትን በማጠናከር

1.6 የትምህርት ቢሮ ራዕይ፣ ተልዕኮና እሴቶች

1.6.1 የሴክተሩ ራዕይ

በአዲስ አበባ ከተማ ውጤታማ የትምህርት ሥርዓት በማስፈን በ2012 ዓ.ም ዓለምዓቀፋዊ ተወዳዳሪ የሆኑ የትምህርት ተቋማትና በልማት' በዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር ግንባታ ቁልፍ ሚና የሚጫወቱ የተሟላ ስብዕና ያላቸው ዜጎች ማፍራት።።

1.6.2 የሴክተሩ ተልዕኮ

የአዲስ አበባ ከተማን ነዋሪ በትምህርት ስራ ላይ በባለቤትነት በማሳተፍ ለትምህርት መዋቅሩ አካላትና በትምህርት መስክ ለተሰማሩ ባለሀብቶች ሙያዊና ቴክኒካል ድጋፍ በመስጠት፣ አጋር ድርጅቶችን በማስተባበር፣የትምህርት ተቋማትን በፍትሓዊነት በማስፋፋት የከተማዋን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ፣ አለምአቀፋዊ ደረጃዉን የጠበቀና በቴክኖሎጂ የተደገፈ ትምህርት በተስማሚ ፕሮግራሞች ለህብረተሰቡ ማድረስ።።

1 6.3የሴክተሩ እሴቶችና የእሴቶች መግለጫ

1. ለትምህርት ጥራት ቅድሚያ መስጠት
2. በመልካም ስነ-ምግባር የታነጹ ዜጎችን ማፍራት
3. በጥናትና ምርምር የትምህርት ችግሮቻችንን መፍታት
4. በጋራ መስራት መገለጫችን ነው
5. ግልፅነት
6. ተጠያቂነት
7. በዕውቀትና በዕምነት መምራት/መስራት
8. የላቀ አገልግሎት መስጠት
9. ለለውጥ ዝግጁነት

1.6.4 የእሴት መግለጫ

1. ለትምህርት ጥራት ቅድሚያ እንሰጣለን

የትምህርት ጥራትን ለመጠበቅ ተማሪዎች በምቹ የትምህርት አካባቢ፣ በተሟላ የትምህርት መሣሪያና ግብአት፣ብቃት ባላቸው መምህራንና የትምህርት አመራሮች ሀገራዊና አለምአቀፋዊ ስታንዳርድ ያሟላ ሥርዓተ ትምህርትና የመማር ማስተማር ስነዘዴን ተግባራዊ በማድረግ ለሀገር ልማት ለመልካም አስተዳደርና ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ዜጎች ለማፍራት ቅድሚያ ሰጥቶ መስራት ማለት ነው፡፡

2. በመልካም ሥነምግባር የታነፁ ዜጎችን እናፈራለን

ወጣቶች የነገ ሀገር ተረካቢና ገንቢ እንደመሆናቸው መጠን የተሟላ ስብዕና ይኖራቸው ዘንድ

- በዕውቀቱና በጉልበቱ ተግቶ የሚሰራ፣
- የራሱንና የሌሎችን መብት አውቆ የሚያከብር፣
- ልዩነቶችንና ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ የሚፈታ፣
- ለፍትሕና ለሚዛናዊነት የሚቆም፣
- በራሱ ማንነትና ብቃት የሚተማመን፣
- ለሀገሪቱ ህጎችና ማህበራዊ ደንቦች የሚገዛ፣
- በህብረተሰቡ ጉዳዮች የሚሳተፍና ኃላፊነት የሚሰማው ዜጋ ለማፍራት ተግተን እንሰራለን ማለት ነው፡፡

3. በጥናት ምርምር የትምህርት ችግሮቻችንን እንፈታለን

ትምህርት በየጊዜው እያደገና እየዳበረ የሚመጣ ከመሆኑ አኳያ ይህን ለውጥ ለማምጣትና የሚከሰቱ ችግሮችን ለመፍታት ጥናትና ምርምር ብቸኛው መንገድ /ዘዴ/ በመሆኑ የትምህርት ተቋማት በዚህ የሚገለገሉ መሆኑን ለማመላከት ነው፡፡

4. በእውቀትና በእምነት እንሰራለን

የእውቀት የአመለካካት፣የክህሎትና የግብዓት አጠቃቀም ችግሮቻችንን በመፍታት አሁን በመቀጣጠል ላይ የሚገኘውን ለውጥ ቀጣይነት በማረጋገጥ የከተማ አስተዳደሩን የልማት፣ የመልካም አስተዳደር እና የዲሞክራሲ ስርአት ግንባታ ለማሳካት ራሳችንን በእውቀት አበልጽገን ሌሎችንም በማሳወቅ በእምነት እና በቁርጠኝነት እንሰራለን፡፡

5. ግልፅነት

በመንግስት ፖሊሲዎች፣ እቅዶች፣ መመሪያዎችና ተግባሮች ላይ ምንጊዜም ነዋሪው ትክክለኛ፣ ወቅታዊና ግልፅ መረጃ እንዲኖረው በማድረግ፣ በህዝብና መንግስት ስራዎች ላይ በበቂ ሁኔታ በመሳተፍ፣ ነዋሪው ከመንግስት የሚያገኘው አገልግሎት ምን እንደሆነ አውቆ እውቀቱን፣ ገንዘቡንና መላ አቅሙን ለልማት ለማዋል እና የመረጠውንም መንግስት ለመቆጣጠር የግልጽነት መርህ አስፈላጊ ነው፡፡ ነገርግን አሰራራችንን ግልፅና አሳታፊ ለማድረግ ጥረት እየተካሄደ ያለ ቢሆንም በቂ ባለመሆኑ በርካታ ህብረተሰቡ ሊሳተፍባቸው የሚገቡ ሆነው ያልተሳተፈባቸው ስራዎች መኖራቸው፣ አንዳንድ ስራዎቻችንም ለህዝብ ግልፅ ባለመሆናቸው ጠቃሚ ሆነው ሳለ እንደማይጠቅሙ አድርጎ የሚያያቸው ጉዳዮች መታየታቸው የግልፅነት አሰራራችን ችግር እንዳለበት ያሳየናል፡፡ በመሆኑም በልማቱም ሆነ በዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ረገድ የህብረተሰቡን ተሳትፎ በሁሉም መስክ ለማጎልበት ግልፅነት ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው በመረዳት፣ በእቅድ አወጣጥ፣አፈጻጸምና ግምገማ ላይ ነዋሪው ሚናውን እንዲወጣ ያልተማከለ አሰራርን በማጠናከር፣ ፍትሀዊ የሆነ የሀብት ባለቤትነትና ተጠቃሚነትን መኖሩን ለማረጋገጥ፣ እንዲሁም በከተማ አስተዳደሩ በሁሉም ደረጃዎች ለስርዓተ ጾታ እኩልነት በጽናት የቆመ አሰራር መኖሩን ለማረጋገጥና ዲሞክራሲያዊ አሰራርን ለማጠናከር የግልፅነትን ስርአት ማጠናከር ወቅታዊ ጥያቄ ነው፡፡

በመሆኑም አመራሩ፣ ሠራተኞችና ነዋሪው በጋራ ጉዳዮች ላይ በመግባባት ልዩነትን በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ ለማቻቻል ለመደማመጥ፣ ስራዎችን ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ለመመዘን እና የበሰለ የዲሞክራሲ ባህል እንዲያብብ ለማድረግ ግልፅነት የተሞላበት አሰራርን ማጠናከር መተኪያ አይገኝለትም፡፡ በመሆኑም የአስተዳደሩን ራዕይና ተልእኮ ለማሳካት፣ ፖሊሲዎች እና ፕሮግራሞችን ለመተግበር እንዲሁም ስትራቴጂካዊ የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ ከተማዊ አቀፍ የጋራ ግንዛቤ መፈጠሩን በማረጋገጥ፣ በልዩነት በማመን የመቻቻል ባህልን ለማዳበር እና ለተልዕኳችን መሳካት ወሳኝ በመሆኑ የግልፅነት መርህን እናጠናክራለን ማለት ነው፡፡

6. ተጠያቂነት

ህዝቦች ባካሄዱት መራራ ትግል የስልጣን ባለቤትነታቸውን አረጋግጠው በዲሞክራሲያዊ ህገመንግስት መመራት ከጀመሩ ጊዜ አንስቶ በርካታ ለውጦች እየተካሄዱ ይገኛሉ፡፡ በዋናነት ይህ መብት በይበልጥ እየተከበረ እንዲሄድ፣የህግ የበላይነትና የዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ በሚፈለገው ደረጃ ላይ እንዲደርስ፣ማንኛውም የመንግስት አካል ህግን መሰረት በማድረግ የሚወስነው ውሳኔም ሆነ የሚያከናውነው ተግባር የዜጎችን ፍላጎት መሰረት ያደረገ እንዲሆን የተጠያቂነት አሰራር ማስፈን ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ ሆኖም ይህ አሰራር በበቂ ሁኔታ በተግባር ላይ ባለመዋሉ ለበርካታ የአሰራር ችግሮች፣ የመንግስትና ህዝብ ሃብት ብክነት የተዳረግንባቸው ሁኔታዎች አሉ፡፡ በመሆኑም ይህ መርህ ማንኛውም ሰው በህግ ፊት እኩል መሆኑንም ጭምር ያረጋገጠና መንግስትም እንዲያስተዳድረው የመረጠው ህዝብ በተስማማባቸው ህጎች

አጥር ውስጥ ሆኖ እንዲሰራ፣የህዝብን ውክልና ያለአግባብ እንዳይጠቀምበት በማድረግ በህዝቡ ይሁንታ ብቻ የሚመራ እንዲሆን የሚያስችል ወሳኝ መሳሪያ ነው።።

በመሆኑምየተጠያቂነት ስርአትን በማጠናከር ስራዎቻችን የሰላም፣ የዲሞክራሲና የልማት ምሶሶዎች እንዲሆኑ ማድረግ ይጠበቃል።። በተጨማሪም አመራሩና ሠራተኛው በስራው ውጤት ተለክቶ የሚፈለገውን ግብ ያስመዘገበ የሚበረታታበት፣ችግሮች በዲሞክራሲያዊ አግባብ የሚስተካከሉበት፣ ከህግ አግባብ ውጪም የተንቀሳቀሰ በህግ የሚጠየቅበት የተጠያቂነት ሥርዓት የስራችን ቁልፍ አድርገን መውሰድ ይገባል።። ስለሆነም የህዝብ አገልግሎት አሰጣጣችን በተጠያቂነት መርህ እንዲታገዝ በማድረግ ምርጥ ተሞክሮ በማስፋፋት፣ የኪራይ ሰብሳቢነትን ፖለቲካል ኢኮኖሚን መሰረት በመናድና ተጠያቂነትን የተቀበለ የልማት ሰራዊት በመፍጠር ልማትን እናፋጥናለን ማለት ነው።።

7. ለለውጥ ዝግጁ ነን

ለውጥ በራሱ የማይቀርና ነባራዊ ጉዳይ ነው።። ሆኖም አለም ከነባራዊው ለውጥ በፈጠነ መልኩ በተለዋዋጭና በማያቋርጥ የለውጥ ሂደት ውስጥ ትገኛለች።። ለዚህም እያንዳንዱ ግለሰብም ሆነ ሃገር ሁለንተናዊና ተስማሚ የለውጥ ቅኝት ማድረግ ካልቻለ በዚች ፈጣን አለም ውስጥ መኖር የማይችልበት ደረጃ ላይ እየተደረሰ ለመሆኑ በርካታ ትርጉም ያላቸው አመላካቾች እየታዩ ናቸው።።

በአንፃሩ ደግሞ በከተማችን ውስጥ ለውጥን በቶሎ ያለመቀበል አመለካከት ጎልቶ የሚታይበት ሁኔታ መኖሩ ስራችንን ከባድ ያደርገዋል።። በመሆኑም በቅድሚያ አመራሩና ሰራተኛው ለለውጥ ግንባር ቀደም እንዲሆን በማድረግ በቀጣይ በአጠቃላይ የከተማችን ነዋሪ ከሚለዋወጠው አለም ሁኔታ ጋር በተመጣጣኝ ደረጃ ለመለወጥ በአመለካከትም ሆነ በተግባር እንዲዘጋጅ ማድረግ ያስፈልጋል።። ስለዚህ ሁሉም የአስተዳደሩ አመራርና ሰራተኞች የአገልጋይነት መንፈስ በማዳበር፣ የስራ ፈጠራ ባህልንና ለውጥን በፍጥነት ተቀብሎ የመስራትና የመምራት አቅምን በማጎልበት ከሚመጣው ለውጥ ሊገኝ የሚችለውን መልካም እድል አሟጠ ለመጠቀም እንዲቻል ለለውጥ ዝግጁ በመሆን ከለውጥ ጋር አብሮ ለመሄድ ተግተን እንሰራለን ማለት ነው።።

8. የላቀ አገልግሎት እንሰጣለን

በአሁኑ ሰአት አገልግሎት አሰጣጣችን እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም ነዋሪው በወቅቱ ከሚፈልገው ዘመናዊ አሰራር አኳያ በርካታ ክፍተቶች ይታያሉ።። በመሆኑም የከተማዋን ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት ያደረገ ሥርነቀል ተቋማዊ የአሰራር ለውጥ በማምጣት ለህዝቡ የልማት ጥያቄ ፈጣን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ አሰራሮችን በማሳደግ፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ አስተዳደር ስርአት በመዘርጋት፣ ቀልጣፋና ተገልጋይ ተኮር የሆነ የላቀ አገልግሎት አሰጣጥ ስርአትን እውን ማድረግ ያስፈልጋል።። የላቀ መንግስታዊ አገልግሎት በከተሞች ያለን የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚን መሰረት ለመናድና በምትኩ የልማታዊ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ መሰረትን ለማስፋት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል።። በተጨማሪም ይህ አሰራር

መንግስት ለልማታዊ ባለሃብቶችና ነዋሪው የሚሰጠውን አገልግሎት ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆን ከማድረጉም በላይ ለልማት ያለው ትርጉም ከፍተኛ በመሆኑ ሲቪል ሰርቪሱ ለተጠቃሚው የላቀ አገልግሎት የመስጠት እሴትን እንደ አንድ ተግባር አደርጎ እንዲወስድ በመድረግ የላቀ አገልግሎት ለህብረተሰቡ ለመስጠት ተግተን እንሰራለን ማለት ነው፡፡

9.በጋራ መስራት መገለጫችን ነው

የትምህርት ስራ የተናጠል ወይም በግለሰብ ደረጃ ብቻ የሚሰራና የሚመራ ሳይሆን በቡድን ተሰርቶ ውጤት የሚታይበት በመሆኑ በትምህርት ተቋማት ይህን በጋራ የመስራት ልምድ ይበልጥ የሚያጠናክሩበትና ውጤት የሚያመጡበት ማለት ነው፡፡

1.7.4. በተቋሙ የተመረጡ ስትራቴጂያዊ እይታዎች

በትምህርት ቢሮ የተመረጡ ስትራቴጂያዊ እይታዎች አራት ሲሆኑ ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡ እነዚህ አራቱ ዕይታዎች ረጅምና አጭር ግቦችን'የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት የሚያስችሉ ክንዋኔዎችን ለማመጣጠንና የተቋሙን ሁኔታ በግልጽ ማየት የሚያስችሉ ናቸው፡፡

ሀ. ህዝብ/ተገልጋይ/CITIZENS/CUSTOMERS

ለ. ፋይናንስ/FINANCE

ሐ. ውስጣዊ አሳራር/INTERNAL BUSINESS PROCESS

መ. መማሪና እድገት/LEARNING AND GROWTH/CAPACITY BUI

ደረጃ ሁለት፡ ተቋማዊ ስትራቴጂ መንደፍ

2.1 ስትራቴጂክትኩረት መስኮችውጤት(Strategic Themes Results)

ተቁ	ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች / Strategic Themes/	የትኩረት መስኮች ውጤት /Strategic Themes Result/
1	ውጤታማ የትምህርት አገልግሎት	ትምህርትን ተደራሽ ፣ፍትሃዊና ጥራቱን የጠበቀ በማድረግ በዕውቀት፣በክህሎት፣በአመለካከት፣በስነምግባሩ የተካነና ችግር ፈቺ የሆነ ዜጋ
2	የትምህርት ዘርፍ የማስፈጸም አቅም ግንባታ	በትምህርት ዘርፍ ውጤታማ አደረጃጀትና አሰራር በመፍጠር ተገቢ ዕውቀት ፣ክህሎትና አመለካከት ያላቸውና ለአፈፃፀም የሚተጉ በየደረጃው ያሉ የትምህርት አመራር ፈጻሚዎችና መምህራን

2.2 የስትራቴጂክትኩረትመስኮችመግለጫ(ጠቀሜታ፣ወሰንናትርጉም) (Strategic Themes Commentary)

በዚህ የስትራቴጂ የትኩረት መግለጫ ለእያንዳንዲ የትኩረት መስክ የስትራቴጂ ውጤት፣ ጠቀሜታ፣ ወሰንና ትርጉም ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስክ	ስትራቴጂያዊ ውጤት /Strategic Result/	ትርጉም /Meaning/
1	ውጤታማ የትምህርት አገልግሎት	ትምህርትን ተደራሽ ፣ፍትሃዊና ጥራቱን የጠበቀ በማድረግ በዕውቀት፣በክህሎት፣በአመለካከት፣በስነምግባሩ የተካነና ችግር ፈቺ የሆነ ዜጋ ማፍራት	ደረጀውን የሚመጥንና ተገቢነት ያለውን እና ችግር ፈቺ የትምህርት ሥርዓት ማስፈን
2	የትምህርት ዘርፍ የማስፈጸም አቅም ግንባታ	በትምህርት ዘርፍ ውጤታማ አደረጃጀትና አሰራር በመፍጠር ተገቢ ዕውቀት ፣ክህሎትና አመለካከት ያላቸውና ለአፈፃፀም የሚተጉ በየደረጃው ያሉ የትምህርት አመራር ፈጻሚዎችና መምህራን	ብቃትያለውየሰውሃይልበቀጣይነትበማፍራት፣አሰራርናአደረጃጀትንበቀጣይነትማሻሻልማለትነው

ደረጃ 3 ፡- ስትራቴጅያዊግቦች (Strategic Objectives)

3.1 የተጠቃለሉ ስትራቴጂያዊ ግቦች

እይታ መስክ	ስትራቴጂያዊ ግቦች	ምርመራ
ህዝብ/ተገልጋይ	1የትምህርት ጥራት ማረጋገጥ	
	2.ውስጣዊ የትምህርት ብቃት ማረጋገጥ	
	3 የትምህርት ፍትሃዊነት ማረጋገጥ	
	4የትምህርት ሽፋንና ተደራሽነት ማሳደግ	
ፋይናንስ	5ውጤታማ የሀብት አጠቃቀምን ማሳደግ	
	6የሀብት ምንጮችን ማስፋት	
ውስጣዊ አሰራር	7ሞዴል የትምህርት ተቋማትን ማሳደግ	
	8የህብረተሰብ ተሳትፎ ማሳደግ	
	9የመረጃ ሽፋን፣ ጥራትና ተደራሽነትን ማሳደግ	
	10.ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ፍትሃዊ አገልግሎት መስጠት	
	11የኪራይሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር መቀነስ	
	12.የማስፋት ስትራቴጂ ተደራሽነትናጥራት ማሳደግ	
	13.የክትትል፣ድጋፍ ግምገማና ግብረ-መልስ ስርዓት ማሻሻል	
	14.የምዘናና የሽልማት አሰራር ማሻሻል	
	15.የባለዘርፉ ብዙ ጉዳዮች አሰራር ስርዓት ማሳደግ	
መማርና እድገት	16.የአመራሩን፣ የመምህሩንና የፈፃሚውን ብቃት ማሳደግ	
	17.የመምህራንና የት/አመራር የሙያ ብቃት ማረጋገጥ	
	18.የትምህርትኢንፎርሜሽን ኮምንኬሽን ቴክኖሎጂ ካፒታል ማሳደግ	

3.2 የስትራቴጂያዊ ግቦች መገለጫ

እይታ	የተጠቃለሉ ስትራቴጅያዊ ግቦች	ወሰን	ምክንያት	ውጤት	ይዘት	ትርጉም
ህዝብ	1 የትምህርት ጥራት ማረጋገጥ	በየደረጃው ያሉ የትምህርት ተቋማት	የትምህርት ጥራት በሚፈለገው ደረጃ አለመሳካት	ሁሉም ተማሪ በስነ-ምግባርና በውጤት ብቁ ሆኖ መገኘት	ደረጃውን የሚመጥን የተከታታይ ምዘናና ፈተና ዝግጅት ሥርዓት ማስፈን	በተቀመጠው ኢላማ መሰረት ወጪ ቆጣቢና ውጤታማ ትምህርት መስጠት ማለት ነው
	2. ውስጣዊ የትምህርት ብቃት ማረጋገጥ	በየደረጃው ያሉ የትምህርት ተቋማት	ውስጣዊ የትምህርት ብቃት በሚፈለገው ደረጃ አለመሳካት	ሁሉም ተማሪ በስነ-ምግባርና በውጤት ብቁ ሆኖ መገኘት	ደረጃውን የሚመጥን የተከታታይ ምዘናና ፈተና ዝግጅት ሥርዓት ማስፈን	በተቀመጠው ኢላማ መሰረት ወጪ ቆጣቢና ውጤታማ ትምህርት መስጠት ማለት ነው
	3.የትምህርት ፍትሃዊነት ማረጋገጥ	የከተማ አስተዳደሩና የሴክተሩ መዋቅር	የልዩ ፍላጎት፣ጎልማሶችና የሴቶች የትምህርት ተሳትፎ በሚፈለው ደረጃ ላይ ተደራሽ አለመሆን	ፍትሃዊ በሆነ የትምህርት አገልግሎት የህብረተሰቡን ፍላጎት ማርካት	ለህብረተሰቡ ፍትሃዊ የትምህርት አገልግሎት መስጠት	ሚዛናዊና ፍትሃዊ በሆነ መልኩ አገልግሎት መስጠት ማለት ነው፡፡
	4.የትምህርት ሽፋንና ተደራሽነት ማሳደግ	የከተማ አስተዳደሩና የሴክተሩ መዋቅር	የትምህርት ሽፋንና ተደራሽነት በሚፈለገው ደረጃ ማድረስ አለመቻል	የትምርት አገልግሎትን ተደራሽ በማድረግ ህብረተሰቡን ማርካት	ለሁሉም ህብረተሰብ የትምህርት አገልግሎት መስጠት	ለሁሉም ዜጋ የትምህርት አገልግሎት በማሳካት የዲሞክራሲ ግንባታ ማሳለጥ ማለት ነው

	5.ውጤታማ የሀብት አጠቃቀምን ማሳደግ	በየደረጃው በሚገኙ የትምህርት ተቋማት	የሃብት አጠቃቀም በሚፈለገው ደረጃ ውጤታማ ሆኖ አለመገኘት	ወጪ ቆጣቢ የሀብት አጠቃቀም ስርዓት በመዘርጋት የተገልጋዩን እርካታ ማረጋገጥ	ገንዘብና ገንዘብ ነክ ያልሆኑ ሃብቶችን ከብክነት በጸዳ መልኩ መጠቀም	ወጪ በመቆጠብና ብክነት በመቀነስ ውጤታማ የትምህርት ተቋማትን መገንባት
	6.የሀብት ምንጮችን ማስፋት	በትምህርት ሴክተሩ በየደረጃው ያለ ተቋማት	የትምህርት አገልግሎቱን ወደ ሚፈለገው ደረጃ ለማድረስ የሃብት መጠን ውስን መሆን፣	በቂ ሃብት በማግኘት ውጤታማ የትምህርት አገልግሎት ማረጋገጥ	ሃብት/የገንዘብ፣የማቴሪያልና የእውቀት - እርዳታ፣ ብድር፣ የህዝብ መዋጮ፣ ስጦታ፣ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት፣ ፈንድ…	የትምህርት ሥራን ለማሳካት የገንዘብ፣ የማቴሪያልና የሰው ሃብትን (የእውቀት) የሃብት ምንጮችን ማስፋት ማለት ነው
	7.ሞዴል የትምህርት ተቋማትን ማሳደግ	የከተማ አስተዳደሩና በየደረጃው ያለው የሴክተሩ ትምህርት ተቋም	በስታንዳርዱ መሰረት ብቃት ያላቸውና ውጤታማ ትምህርት ተቋማት መገንባት ባለመቻሉ	ከፍተኛ የተገልጋይ እርካታ	በስታንዳርዱ መሰረት ውስጣዊና ውጫዊ ግብዓትና አሰራር ማሻሻል፡፡	በስታንዳርዱ መሰረት ደረጃ 3ና4/በአፈጻጸም ምዘና ውጤት 80ና ከዚያ በላይ ያስመዘገቡ ተቋማት

	8.የህብረተሰብ ተሳትፎ ማሳደግ	የከተማው ሕብረተሰብ	የትምህርት የፖ'ሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎች' ፓኬጅ እና እቅዶችን ዝግጅት፣ ትግበራና ግምገማ ላይ የተደራጅ የህዝብ ተሳትፎ ዝቅተኛ መሆኑ፣ በትምህርት ሥርዓቱ የህዝብ ተሳትፎና የባለቤትንት ስሜት አናሳ መሆኑ	በትምህርት ሥርዓቱ የሕዝብ ሁለንተናዊ ተሳትፎ በማሳደግ ችግሮችን መቅረፍ	-የህዝብ አደረጃጀት ለግንዛቤ፣ለፖ'ሊሲናስት ራቴጂ፣ ለእቅድ ዝግጅት፣ ትግበራና ክትትልና ግምገማ የተዘጋጁመድረኮች የህብረተሰብ ተሳትፎ የወላጅ ተሳትፎ	ህዝቡ በትምህርት ዘርፉ ያለውን ሃሳብን ከማመንጨት ጀምሮ በእውቀቱ፣ በገንዘቡና፣ በጉልበቱ ቀጥተኛ ተሳታፊ የመሆንና ውሳኔዎች ላይ ተጽእኖ የማሳደር ሰፊ ድርሻ እንዲኖረው ማድረግ ማለት ነው፡፡
	9.የመረጃ ሽፋን፣ ጥራትና ተደራሽነትን ማሳደግ	በከተማ አስተዳደሩናበሴክተሩ በየደረጃው የሚገኙ የትምህርት ተቋማት	-ለህብረተሰቡም ሆነ ለትምህርት ባለድርሻ አካላትና አጋሮች ወቅታዊና ተዕማኒ መረጃ ማግኘት ላይ እጥረት መኖሩ፣ -የመረጃ ጥራትና ተደራሽነት በሚፈለገው ደረጃ ላይ ያለመድረስ	ወቅታዊ፣ተዓማኒና ተደራሽ የሆነ መረጃ አቅርቦት ማረጋገጥ	-የመረጃ ሽፋን፣ ጥራት፣ተደራሽት -ወቅታዊ መረጃ -የተለያዩ ሚዲያዎች -በድረ-ገጽ የተሰራጨ መረጃ	በትምህርት አገልግሎት ጥቅም ላይ የሚውሉ የተለያዩ መረጃዎችን በጥራት ተደራሽ ማድረግ ማለት ነው

	10.ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ፍትሃዊ አገልግሎት መስጠት	በየደረጃው በሚገኙ የትምህርት ተቋማት	የአገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋና ውጤታማነት በየጊዜው እያደገ ከሚሄደው የተገልጋዮች ፍላጎት ጋር ያለመጣጣም	የተገልጋዮችን የእርካታ ደረጃ ከፍ ማድረግ	-አገልግሎት ሠጪ ተቋማት -የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ -የተገልጋዮች ፍላጎት	ከጊዜ ፣ጥራት፣ወጪና ከእርካታ እንዲሁም ከግብ ስኬት አኳያ የተገልጋዮችን ፍላጎት የሚያሟላ አገልግሎት ማቅረብ ማለት ነው፡፡
	11.የኪራይሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር መቀነስ	በየደረጃው በሚገኙ የትምህርት ተቋማት	የትምህርት ማህበረሰቡ ኪራይ ሰብሳቢነትን በጽናት የመታገል ልምዱ ዝቅተኛ መሆን	ኪራይ ሰብሳቢነትን በፅናት የሚታገል ዜጋ	- የኪራይ ሰብሳቢነት ባህሪን የሚፀየፍ የትምህርት አመራርና ፈጻሚ /ግንባር ቀደም/ ማበራከት -የመተጋገል፣ የመጠቆም ፣ለህግ የማቅረብ... ባህል ማሳደግ	የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ በመድፈቅ የልማታዊ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አስተሳሰብ ማረጋገጥ ማለት ነው፡፡
	12. የማስፋት ስትራቴጂ ተደራሽነትና ጥራት ማሳደግ	በየደረጃው በሚገኙ የትምህርት ተቋማት	ተሞክሮዎችን በመለየት፣በመቀመርና በማስፋት ረገድ ያለው አሰራር በሚፈለገው ደረጃ አለመሆን፣	የላቀና ውጤታማ ተሞክሮዎችን በመቀመርና በማስፋፋት አፈጻጸማቸው ከፍ ያለ የትምህርት ተቋማት	መለየት መቀመር ማስፋፋት	በተግባር ላይ ውለው የተሻለ ውጤት የተገኘባቸውን ምርጥ አሰራሮች፣አደረጃጀቶችና ቴክኖሎጂዎች በማስፋፋት ከራስ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ የመቀመርና ለላቀ ውጤት ማብቃት ማለት ነው፡፡

የውስጥ አሰራር	13.የክትትል፣ድጋፍ ግምገማና ግብረ-መልስ ስርዓት ማሻሻል	በሴክተሩ በየደረጃው በሚገኙ የትምህርት ተቋማት	የሱፐርቪዥን፣ክትትልና ግምገማ ስርዓት ውጤታማነቱ ዝቅተኛ መሆን	ውጤታማ የእቅድ አፈጻጸም ያላቸው የትምህርት ተቋማት	ክትትልና ድጋፍ፣ ሪፖርት፣ የአካል ግምገማ ግብረመልስ	ሶስቱንም የክትትልና ድጋፍ መስተጋብሮች በመጠቀም ውጤታማ የትምህርት ተቋማትን መገንባት ማለት ነው
	14.የምዘናና የሽልማት አሰራር ማሻሻል	በከተማ አስተዳደሩና በየደረጃው የሚገኙ የትምህርት ተቋማት	ውጤትን መሰረት ያደረገ የምዘና፣እውቅናና ሽልማት ስርዓት አለመገንባት	ጤናማ የውድድር መንፈስ የሚፈጥርና ተጠያቂነት የሚያሰፍን አሰራር በመዘርጋት የላቀ አፈጻጸም ያላቸው ተቋማት፣አመራርና ፈጻሚዎች መፍጠር	-የምዘና ደንቦች፣መመሪያዎችና ማንዋሎች፣ -የቅሬታ ማስተናገጃ ስርዓት፣ -ተመዛኝ ተቋማት፣ አመራርና ፈጻሚ ስታንዳርድ -የሽልማት ስርዓትና ማበረታቻ -የምዘና ውጤት	ተቋማት፣ አመራሩ እና ፈጻሚዎች የትምህርት-ተቋማትን ተልዕኮ በማስፈጸም ሂደት በዕቅድ አፈጻጸማቸው ባስመዘገቡት ውጤት መሰረት የእውቅና እና የተጠያቂነት ሥርዓት መዘርጋት ማለት ነው፡
	15.የባለዘርፉ ብዙ ጉዳዮች አሰራር ስርዓት ማሳደግ	በከተማ አስተዳደሩና በየደረጃው የሚገኙ የትምህርት ተቋማት	ሁሉም ባለድርሻ አካላት በባለዘርፉ ብዙ ጉዳዮች ተቀናጅቶ በመስራት የሚጠበቀውን ያህል ውጤታማ አለመሆን፤	በባለ ዘርፉ ብዙ ጉዳዮች ትስስራዊ አሰራር በማጎልበት ውጤታማ የ ትምህርት አገልግሎት መስጠት	ከባለ ድርሻ አካላት ጋር ትስስር፣ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ፣የትስስር አሰራር ፣ህብረተሰቡና ልማታዊ ባለሃበት የውስጥና የውጭ ትስስር	የትምህርት ሴክተሩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻና ተባባሪ አካላት ጋር የተቀናጀ የአሰራር ስርዓት መዘርጋትና የባለ ዘርፉ ብዙ ጉዳዮችን አካቶ የመስራት አሰራርን ማሳደግ ማለት ነው፡፡

	17.የመምህራንና የት/አመራር የሙያ ብቃት ማረጋገጥ	የትምህርት ሚኒስቴርና በየደረጀው ያሉ ተቋማት	የመምህራን ብቃትና ስነ-ምግባር ሰታንዳርዱን መጠበቅ ባለመቻሉ	ተወዳዳሪና ብቃት ያላቸው መምህራን ማግኘት	ሀገር አቀፍ የመምህራንና ትምህርት አመራር ብቃት መስጫ ስታንዳርድ	ሙያዊ ብቃታቸው የተረጋገጠላቸው የትምህርት አመራርና መምህራን
	18.የትምህርትኢንፎር ሜሽን ኮምንኬሽን ቴክኖሎጂ ካፒታል ማሳደግ	በከተማ አስተዳደሩና በየደረጃው በሚገኙ ተቋማት	የዘመናዊ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ክህሎት ክፍተት መኖር	የዳበረ ዘመናዊ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በማሳደግ ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት መስጠት	የኢንፎረሜሽን ኮሙኒኬሽን መሠረተ ልማት፣ አውቶሜሽን፣ኢንተር ኔት ኢንትራ ኔት፣ የተለያዩ ሶፍትዌሮች፣ኮምፒውተር፣የተለያዩ ዌብሳይቶችን ፣ ጥገና፣ ስልጠና	የተለያዩ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በመጠቀም ዘመናዊ አሰራሮችን በማጎልበት ውጤታማ መሆን ማለት ነው

ደረጃ 4 ፡- ስትራቴጅያዊ ማፕ (Strategic Mapping)

ስትራቴጅያዊ ማፕ የግቦች ተመጋጋቢነት የሚታይበትና ስትራቴጂው በአጭሩ የሚተረክበት ስዕላዊ መግለጫ ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ስር የትምህርት ሴክተሩ የተጠቃለለ ስትራቴጂ ማፕ በምክንያትና ውጤት ተሳስሮ ቀርቧል፡፡

4.1. የተጠቃለለ የትምህርት ሴክተሩ ስትራቴጂያዊ ማፕ (Corporate Map)


ዕይታ
ስትራቴጂያዊ ግቦች
ህዝብ /ተገልጋይ /Citizens/
የትምህርት ጥራት ማሻሻል
የትምህርት ሽፋንና ተደራሽነት
የትምህርት ብቃት
የትምህርት ፍትሀዊነት
ፋይናንስ
ውጤታማ የሀብት አጠቃቀምን ማሳደግ
የሀብት ምንጮችን


ውስጣዊ አሰራር
ሞዴል የትምህርት ተቋማትን ማሳደግ
የኪራይሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር መቀነስ
ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ፍትሃዊ አገልግሎት መስጠት
የመረጃ ሽፋን፣ ጥራትና ተደራሽነትን ማሳደግ
የክትትል፣ድጋፍ ግምገማና ግብረ-መልስ ስርዓት ማሻሻል
የማስፋት ስትራቴጂ ተደራሽነትናጥራት ማሳደግ
የምዘናና የሽልማት አሰራር ማሻሻል
የባለዘርፉ ብዙ ጉዳዮች አሰራር ስርዓት ማሳደግ
መማርና እድገት
የመምህራንና የት/አመራር የሙያ ብቃት ማረጋገጥ
የአመራሩን፣ የመምህሩንና የፈፃሚውን ብቃት ማሳደግ
የትምህርትኢንፎርሜሽን ኮምንኬሽን ቴክኖሎጂ ካፒታል ማሳደግ

ደረጃ አምስት፤- ስራቴጂያዊ መለኪያዎችና ኢላማዎች

5.1 ስትራቴጅያዊ ግቦችና መለኪያዎችን ለማስቀመጥ የተዘጋጀ የመረጃ ማብራሪያ

የእይታ መስክ	ስትራቴጂያዊ ግቦች/Strategic Objectives/	መለኪያ/Measures/	ዳታ			የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ /Methodology/	ቀመር	የቀመር መገለጫ	የመረጃው ትክክለኛነት ያረጋገጠው /Validation
			ምንጭ /Source/	ጥራት /Quality/	የክለሳ ጊዜ /Data update rate/				
ህዝብ /ተገልጋይ	1 የትምህርት ጥራት ማረጋገጥ	በ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና አማካይ ውጤት 50%ና በላይ ያመጡ ተማሪዎች በመቶኛ	የትምህርት ጥናት ምርምር ፈተናና ምዘና ስራሂደት/የእቅድ ጥናት በጀት ደጋፊ ስራሂደት	ከፍተኛ	በየአመቱ	በሪፖርት	ሀ/ለ(100)	ሀ=በ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና አማካይ ውጤት 50%ና በላይ ያመጡ ተማሪዎችለ=አጠቃላይ 8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና የወሰዱ ተማሪዎች ብዛት	የትምህርት ጥናት ምርምር ፈተናና ምዘና ስራሂደት
		በ10ኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተና 2፡00 እና ከዚያ በላይ ያመጡ ተማሪዎች በመቶኛ	የትምህርት ጥናት ምርምር ፈተናና ምዘና ስራሂደት/የእቅድ ጥናት በጀት ደጋፊ ስራሂደት	ከፍተኛ	በየአመቱ	በሪፖርት	ሀ/ለ(100)	ሀ= በ10ኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተና 2፡00 እና ከዚያ በላይ ያመጡ ተማሪዎች ብዛት ለ= አጠቃላይ የ10ኛ ብሄራዊ ፈተና የወሰዱ ተማሪዎች ብዛት	የምዘና ናፈተናዎች ኤጀንሲ
		በ12ኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተና ውጤት 350 እና ከዚያ በላይ ያመጡ ተማሪዎች በመቶኛ	የትምህርት ጥናት ምርምር ፈተናና ምዘና ስራሂደት/የእቅድ ጥናት በጀት ደጋፊ ስራሂደት	ከፍተኛ	በየአመቱ	በሪፖርት	ሀ/ለ(100)	ሀ = በ12ኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተና ውጤት 350 እና ከዚያ በላይ ያመጡ ተማሪዎች ለ= አጠቃላይ 12ኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተና የወሰዱ ተማሪዎች ብዛት	የምዘና ናፈተናዎች ኤጀንሲ

		በክፍል የፈተና ውጤት አማካይ 50% እናበላይያመጡ ተማሪዎች በመቶኛ	የትምህርት ጥናት ምርምር ፈተናና ምዘና ስራሂደት/የእቅድ ጥናት በጀት ደጋፊ ስራሂደት	ከፍተኛ	በየ ግማሽ አመቱ	በሪፖርት	ሀ/ለ(100)	ሀ = በክፍል የፈተና ውጤት አማካይ 50% እናበላይያመጡተማሪዎች ብዛት ለ= አጠቃላይ	የትምህርት ጥናት ምርምር ፈተናና ምዘና ስራሂደት
		የትምህርት ቅበላ ጥናት ውህድ (proffecient) ውጤት በመቶኛ	የትምህርት ጥናት ምርምር ፈተናና ምዘና ስራሂደት/የእቅድ ጥናት በጀት ደጋፊ ስራሂደት	ከፍተኛ	በየሁለት አመቱ	በሪፖርት	ሀ/ለ(100)	ሀ = የትምህርት ቅበላ ጥናት ውህድ ፈተና ወስደው አጥጋቢ ውጤት ያገኙ ተማሪዎች ብዛት ለ= አጠቃላይ የትምህርት ቅበላ ጥናት ውህድ ፈተና የወሰዱ ተማሪዎች	እቅድ ጥናት በጀት ደጋፊ ስራሂደት
		ለየእርከን ደረጃው የሚመጥኑ የመምህራን በመቶኛ	የመምህራንናትምህርት አመራር ልማት ዋና የስራ ሂደት	ከፍተኛ	በየአመቱ	ሪፖርት	ሀ/ለ(100)	ሀ= ለእርከኑ የሚመጥኑ መምህራን ብዛት ለ= አጠቃላይ በእርከኑ ደረጃ ያሉ መምህራን	የመምህራንና ትምህርት አመራር ልማት ዋና የስራ ሂደት
	2.ውስጣዊ የትምህርት ብቃት ማረጋገጥ	መጠነ ማቋረጥ በመቶኛ	የትምህርት ጥናት ምርምር ፈተናና ምዘና ስራሂደት/የእቅድ ጥናት በጀት ደጋፊ ስራሂደት	ከፍተኛ	በየአመቱ	ሪፖርት	ሀ/ለ(100)	ሀ= ያቋረጡ ተማሪዎች ብዛት ለ =አጠቃላይ የተመዘገቡ ተማሪዎች ብዛት	የትምህርት ጥናት ምርምር ፈተናና ምዘና ስራሂደት/የእቅድ ጥናት በጀት ደጋፊ ስራሂደት

		መጠነ መድገም በመቶኛ	የትምህርት ጥናት ምርምር ፈተናና ምዘና ስራሂደት/የእቅድ ጥናት በጀት ደጋፊ ስራሂደት	ከፍተኛ	በየአመቱ	ሪፖርት	ሀ/ለ(100)	ሀ= የደገሙ ተማሪዎች ብዛት ለ =አጠቃላይ ለፈተና የተቀመጡ ተማሪዎች ብዛት	የትምህርት ጥናት ምርምር ፈተናና ምዘና ስራሂደት/የእቅድ ጥናት በጀት ደጋፊ ስራሂደት
		የማጠናቀቅ ምጣኔ/Completion Rate/ በመቶኛ	የትምህርት ጥናት ምርምር ፈተናና ምዘና ስራሂደት/የእቅድ ጥናት በጀት ደጋፊ ስራሂደት	ከፍተኛ	በየአመቱ	ሪፖርት	ሀ/ለ(100)	ሀ=በእርከኑመጀመርያ የተመዘገቡ ተማሪዎች ብዛት ለ =በእረከኑ መጨረሻ ያጠናቀቁ ተማሪዎች ብዛት	የትምህርት ጥናት ምርምር ፈተናና ምዘና ስራሂደት/የእቅድ ጥናት በጀት ደጋፊ ስራሂደት
	3.የትምህርት ፍትሃዊነት ማረጋገጥ	ጾታዊ ንጽጽር	የእቅድ ጥናት በጀት ደጋፊ ስራ ሂደት/ስርዓተ ፆታ ማስረፅ ትምህርት ክፍል	ከፍተኛ	በየአመቱ	ሪፖርት	ሀ/ለ(100)	ሀ= በመማር ላይ ያሉ ሴት/ወንድ ተማሪዎች ብዛት ለ=በአጠቃላይ መማር የሚገባቸው ሴት/ወንድ ተማሪዎች ብዛት	የእቅድ ጥናት በጀት ደጋፊ ስራ ሂደት/ስርዓተ ፆታ ማስረፅ ክፍል
		የትምህርት እድል ያገኙ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ብዛት	የእቅድ ጥናት በጀት ደጋፊ ስራ ሂደት	ከፍተኛ	በየአመቱ	ሪፖርት	ሀ	ሀ=ልዩፍላጎትያላቸው በመማር ላይ የሚገኙ ተማሪዎች ብዛት	የእቅድ ጥናት በጀት ደጋፊ ስራ
		በተቀናጀተግባርተኮርየጎል ማሶችትምህርትበመማርላይየሚገኙጎልማሶች በመቶኛ	የእቅድ ጥናት በጀት ደጋፊ ስራ ሂደት	ከፍተኛ	በየሩብ አመቱ	ሪፖርት	ሀ/ለ(100)	ሀ.በመማር ላይ ያሉ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ተማሪዎች ብዛትለ=በአጠቃላይ መማር የሚገባቸው የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ብዛት	የእቅድ ጥናት በጀት ደጋፊ ስራ

	4.የትምህርት ሽፋንናተደራሽነት ማሳደግ	የቅድመ መደበኛ ጥቅል ተሳትፎ በመቶኛ	የእቅድ ጥናት በጀት ደጋፊ ስራ ሂደት	ከፍተኛ	በየሩብ አመቱ	ሪፖርት	ሀ/ለX100	ሀ=በመማር ላይ ያሉ የአፀደ ህጻናት ተማሪዎች ብዛት ለ=የቅድመ መደበኛ ትምህርት መማር የሚገባቸው ሕፃናት ብዛት(በመማር ላይ ያሉና + ከት/ቤት ውጪ)	የእቅድ ጥናት በጀት ደጋፊ ስራ
		የ1ኛ ክፍል ንጥር ቅበላ በመቶኛ	የእቅድ ጥናት በጀት ደጋፊ ስራ ሂደት	ከፍተኛ	በየአመቱ	ሪፖርት	ሀ/ለX100	ሀ= በመማር ላይ ያሉ 7 ዓመት የሞላቸው ህፃናት ብዛት ለ= በአጠቃላይ በከተማዋ 7 ዓመት የሞላቸው ህፃናት	የእቅድ ጥናት በጀት ደጋፊ ስራ
		የመጀመሪያ ደረጃ ንጥር ተሳትፎ በመቶኛ	የእቅድ ጥናት በጀት ደጋፊ ስራ ሂደት	ከፍተኛ	በየአመቱ	ሪፖርት	*ሀ/ለX100*	ሀ= በመማር ላይ ያሉ 7-14 ዓመት የሞላቸው ህፃናት ብዛት ለ= በአጠቃላይ በከተማዋ 7-14 ዓመት የሞላቸው ህፃናት ብዛት	የእቅድ ጥናት በጀት ደጋፊ ስራ
		የሁለተኛ ደረጃ (9-10) ጥቅል ተሳትፎ በመቶኛ	የእቅድ ጥናት በጀት ደጋፊ ስራ ሂደት	ከፍተኛ	በየአመቱ	ሪፖርት	*ሀ/ለX100*	ሀ= በሁለተኛ ደረጃ በመማር ላይ ያሉ ተማሪዎች ብዛት ለ= በአጠቃላይ በከተማዋ 15-16ዓመት የሞላቸው ልጆች ብዛት	የእቅድ ጥናት በጀት ደጋፊ ስራ

		የመሰናዶ ት/ት ቅበላ በቁጥር	የእቅድ ጥናት በጀት ደጋፊ ስራ ሂደት	ከፍተኛ	በየአመቱ	ሪፖርት	ሀ	ሀ=ወደ መሰናዶ የገቡ ተማሪዎች ብዛት	የእቅድ ጥናት በጀት ደጋፊ ስራ
		የተገነቡ የትምህርት ተቋማት ብዛት	የእቅድ ጥናት በጀት ደጋፊ ስራ ሂደት	ከፍተኛ	በየአመቱ	ሪፖርት	ሀ	ሀ=ተጨማሪ የተገነቡ መማሪያ ክፍሎች ብዛት	የእቅድ ጥናት በጀት ደጋፊ ስራ
ፋይናንስ	5.ውጤታማ የሀብት አጠቃቀምን ማሳደግ	የንብረትአያያዝናአጠቃቀ ምውጤታማነትበመቶኛ	ጠ/አ/ን/አስተዳደር ደጋፊ የስራሂደት	ከፍተኛ	በየሩብ አመቱ	ሪፖርት/የገቢ ና ወጪ ሞዴሎች	ሀ/ለX100	ሀ=የንብረት አያያዝን ውጤታማ ለማድረግ የተከናወኑ ተግባራት ለ=አጠቃላይ የንብረት አያያዝን ውጤታማ ለማድረግ መከናወን ያለባቸው ተግባራት	ጠ/አ/ን/አስተዳደር ደጋፊ የስራሂደት
		በእቅዱ መሰረት ስራ ላይ የዋለ በጀት በመቶኛ	ጥናት እቅድና በጀትደ/ስ/ሂደት	ከፍተኛ	በየሩብ አመቱ	ሪፖርት/IBEX	ሀ/ለX100	ሀ=ስራ ላይ የዋለ በጀት ለ=በአጠቃላይ የተመደበ በጀት	ጥናት እቅድና በጀትደ/ስ/ሂደት
		የውስጥ አዲት ሽፋን ያገኙ በመቶኛ	የውስጥ አዲት ደጋፊየስራሂደት	ከፍተኛ	በየሩብ አመቱ	የአዲት ሪፖርት	ሀ/ለ(100)	ሀ=የውስጥ አዲት ሽፋን ያገኙ ተቋማት ብዛት ለ=አጠቃላይ አዲት ሽፋን ማግኘት ያለባቸው	የቢሮ ኃላፊዎች

	6.የሀብት ምንጮችን ማስፋት	የሀብትምንጭለማፈላለግየ ተዘጋጁፕሮጀክቶች/የበለፀ ጉ ጥናቶች-ብዛት	ጥናት እቅድና በጀትደ/ስ/ሂደት	ከፍተኛ	በየአመቱ	ሪፖርት	ሀ	ሀ=የሀብት ምንጮችን ለማፈላለግ የተዘጋጁ ፕሮጀክቶች/ጥናቶ ች ብዛት	ጥናት እቅድና በጀትደ/ስ/ሂ ደት
		ለትምህርት ልማት የተሰበሰበ የሀብት መጠን በብር	ጥናት እቅድና በጀትደ/ስ/ሂደት	ከፍተኛ	በየአመቱ	ሪፖርት	ሀ	ሀ=በኅብረተሰብ በመያዶችና ሌሎች ተሳተፎ ለልማት የተሰበሰበሰ የሀብት መጠን በብር	ጥናት እቅድና በጀትደ/ስ/ሂ ደት
ውስ ጣዊ አሰራ ር	7.ሞዴል የትምህርት ተቋማት ማሳደግ	ስታንዳርዱን ያሟላ ትምህርት ተቋማት በመቶኛ	የትም/ጥራት ኢንሰፔክሽን ዋና የስራሂደት	ከፍተኛ	በየ አመቱ	ሪፖርትና ግብረ-መልስ	ሀ/ለ(100)	ሀ=በስታንዳርዱ መሰረት ደረጃ 3 እና 4 ያሟሉ ተቋማት ብዛት ለ=አጠቃላይ የትምህርት ተቋማት ብዛት	የቢሮ ኃላፊዎች
		በአፈጻጸም ምዘና ውጤት 80% እና ከዚያ በላይ ያመጡ የትምህርት ተቋማት በመቶኛ	የለውጥስራዎች/አ/አ/ክትትል ምዘና ንዑስ የስራ ሂደት	ከፍተኛ	በየ አመቱ	የምዘና ውጤት	ሀ/ለ(100)	ሀ=በአፈጻጸም ምዘና ውጤት 80% እና ከዚያ በላይ ያመጡ የትምህርት ተቋማት-ብዛት ለ=አጠቃላይ የትምህርት ተቋማት ብዛት	የቢሮ ኃላፊዎች
	8.የህብረተሰብ ተሳትፎ ማሳደግ	ከህብረተሰብ ጋር በጋራ የተማሪዎች ውጤትና ስነ ምግባር ለማሻሻል የተቀየሱ ስልቶች ብዛት	ጥናት እቅድና በጀትደ/ስ/ሂደት/የ ኮምኒኬሽን ግ/ደ/ስ/ሂደት	ከፍተኛ	በግማሽ አመት	ሪፖርት/ቃለ-ጉባኤ	ሠ	ሀ=የተማሪዎች ውጤትና ስነ ምግባር ለማሻሻል ተግባራዊ የተደረጉ ስልቶች ብዛት	ጥናት እቅድና በጀትደ/ስ/ሂ ደት

		በትምህርት ልማት የተሳተፈ ህብረተሰብ ብዛት	ጥናት እቅድና በጀትደ/ስ/ሂደት/የ ኮምኒኬሽን ግ/ደ/ስ/ሂደት	ከፍተኛ	በግማሽ አመት	ሪፖርት/ቃለ-ጉባኤ	ሀ	ሀ=በትምህርት ልማት የተሳተፈ ህብረተሰብ ብዛት	ጥናት እቅድና በጀትደ/ስ/ሂ ደት
		በህብረተሰብ ተሳትፎ የተሰሩ የልማት ሥራዎች ብዛት	ጥናት እቅድና በጀትደ/ስ/ሂደት/የ ኮምኒኬሽን ግ/ደ/ስ/ሂደት	ከፍተኛ	በግማሽ አመት	ሪፖርት/ቃለ-ጉባኤ	ሀ	የተሰሩ የልማት ስራዎች ብዛት	ጥናት እቅድና በጀትደ/ስ/ሂ ደት
	9.የመረጃ ሽፋን፣ ጥራትና ተደራሽነትን ማሳደግ	ቴክኖሎጂ በመጠቀም ጥራቱ የተጠበቀ መረጃ አቅርቦት በመቶኛ	ጥናት እቅድና በጀትደ/ስ/ሂደት/የ ኮምኒኬሽን ግ/ደ/ስ/ሂደት የኢ.ኮ.ቴ ንዑስ የስራ ሂደት	ከፍተኛ	በግማሽ አመት	ሪፖርት/ድረ-ገጽ/ዳታ ቤዝ	ሀ/ለ(100)	ሀ= ቴክኖሎጂ በመጠቀም በወቅቱ የተሰበሰበና የተሰራጨ መረጃ ብዛት ለ =አጠቃላይ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ለመሰብሰብና ለማሰራጨት የታቀዱ መረጃዎች ብዛት	ጥናት እቅድና በጀትደ/ስ/ሂ ደት/የኮምኒኬ ሽን ግ/ደ/ስ/ሂደት የኢ.ኮ.ቴ ንዑስ የስራ ሂደት
		የለውጥ ኮምንኬሽን ስራዎች ብዛት	ኮሚኒኬሽን/ጉ/ደ/የ ስራሂደት እና የሰው ሃይል አስ/ደ/ስ/ሂደት	ከፍተኛ	በግማሽ አመት	ሪፖርት	ሀ	ሀ=የለውጥ ኮምንኬሽን ስራዎች ብዛት	ኮሚኒኬሽን/ ጉ/ደ/የስራሂደ ት እና የሰው ሃይል አስ/ደ/ስ/ሂደ ት

	10.ቀልጣፋ ውጤታማና ፍትሃዊ አገልግሎት መስጠት	በተቀመጠው ስታንዳርዱ መሰረት አገልግሎት የሰጡ ተቋማት በመቶኛ	የለውጥስራዎች/አ/አ/ክትትል ምዘና ንዑስ የስራ ሂደት	ከፍተኛ	በግማሽ አመት	ሪፖርት	ሀ/ለ(100)	ሀ= በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት አገልግሎት የሰጡ የትምህርት ተቋማት ብዛት ለ=በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት አገልግሎት መስጠት ያለባቸው የትምህርት ተቋማት ብዛት	የቢሮ ኃላፊዎች
		በተሰጡ አገልግሎቶች የረካ ተገልጋይ በመቶኛ	የሰው ሀይል ደ/ስ/ሂደት	ከፍተኛ	በግማሽ አመት	ሪፖርት	ሀ/ለ(100)	ሀ=እርካታቸውን የገለጹ ተገልጋዮች ብዛት ለ=በአጠቃላይ አስተያየት የሰጡ ተገልጋዮች ብዛት (በናሙና ጥናቱ የተዳሰሱ ተገልጋዮች ብዛት)	የቢሮ ኃላፊዎች
		በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ከቀረቡ ቅሬታዎች ውስጥ ምላሽ የተሰጣቸው በመቶኛ	የሰው ሀይል ደ/ስ/ሂደት	ከፍተኛ	በግማሽ አመት	ሪፖርት	ሀ/ለ(100)	ሀ=ከቀረቡ ቅሬታዎቸ ውስጥ ምላሽ የተሰጣቸው ለ=በአጠቃላይ የቀረቡ ቅሬታዎች	የቢሮ ኃላፊዎች

	11.የኪራይሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር መቀነስ	ኪራይ ሰብሳቢነትን ለማክሰም የተቀየሱ ስልቶች ብዛት	በሁሉም ተቋማት	**ከፍተኛ**	በግማሽ አመት	ሪፖርት	*ሀ*	*ሀ=*ኪራይ ሰብሳቢነትን ለማክሰም ተግባራዊ የተደረጉ ስልቶች ብዛት	በየደረጃው ያሉ አመራሮችና የስነ-ምግባር መኮንን
		በኪራይ ሰብሳቢነት ውስጥ ገብተው ተጠያቂ የሆኑ አመራርና ፈጻሚ በመቶኛ	በሁሉም ተቋማት	**ከፍተኛ**	በግማሽ አመት	ሪፖርት	*ሀ /ለ*	*ሀ=*በኪራይ ሰብሳቢነት ውስጥ ገብተው ተጠያቂ የሆኑ አመራርና ፈጻሚ ብዛት *ለ= አጠቃላይ* ኪራይ ሰብሳቢነት ውስጥ የገቡ	በየደረጃው ያሉ አመራሮችና የስነ-ምግባር መኮንን
		ደንብና መመሪያውን ተከትለው የተፈጸሙ ግዥዎች በመቶኛ	እቅድና ግዢ ደ/ስ/ሂደት	**ከፍተኛ**	በየሩብ አመቱ	ሪፖርት	ሀ/ለ(100)	ሀ=ደንብና መመሪያውን ተከትለው የተፈጸሙ ግዥዎች ብዛት ለ=አጠቃላይ የተፈፀመ ግዢ	የቢሮ ኃላፊዎች
	12. የማስፋት ስትራቴጂ ተደራሽነትናጥራት ማሳደግ	ውጤታማነታቸው በተግባር የተፈተሸ ምርጥ ተሞክሮች ብዛት	የለውጥስራዎች/አ/አ/ክትትል ምዘና ንዑስ የስራ ሂደት	**ከፍተኛ**	በየአመመቱ	ሪፖርትናየምርጥ ተሞክሮ ሰነድ	*ሀ*	ሀ=ውጤታማነታቸው በተግባር የተፈተሸ ምርጥ ተሞክሮች ብዛት	የቢሮ ኃላፊዎች
		የተስፋፉ ምርጥ ተሞክሮዎች ብዛት	የለውጥስራዎች/አ/አ/ክትትል ምዘና ንዑስ የስራ ሂደት	**ከፍተኛ**	በየአመመቱ	ሪፖርትናየምርጥ ተሞክሮ ሰነድ	ሀ	ሀ=የተስፋፉ ምርጥ ተሞክሮዎች ብዛት	የቢሮ ኃላፊዎች

	13.የድጋፍና ክትትል፣ ፣ ግምገማና ግብረ-መልስ ስርዓትን ማሻሻል	ድጋፍናክትትል የተደረገላቸው የትምህርት ተቋማት በመቶኛ	የመምህራንና ትምህርት አመራር ልማት ዋና ስራ ሂደት/የለውጥ/ስራ ዎች/ አ/አ/ክትትል ምዘና ንዑስ የስራ ሂደት	ከፍተኛ	በየሩብ አመቱ	ሪፖርትና ግብረ መልስ	ሀ/ለ(100)	ሀ= የክትትልና ድጋፍ የተደረገላቸው ተቋማት ብዛት ለ = አጠቃላይ የተቋማት ብዛት	የትም/ጥራት ኢንስፔክሽን ዋና የስራሂደት
		በስታንዳርዱ መሰረት የኢንስፔክሽን ሽፋን በመቶኛ	የትም/ጥራት ኢንስፔክሽን ዋና የስራሂደት	ከፍተኛ	በየ አመቱ	ሪፖርትና ግብረ መልስ	ሀ/ለ(100)	ሀ=የተደረገ ኢንስፔክሽን/ቁጥጥር ብዛት ለ = የታቀደ ኢንስፔክሽን/ቁጥጥር ብዛት	የትም/ጥራት ኢንስፔክሽን ዋና የስራሂደት
		የትምህርት ሱፐርቪዥን አገልግሎት ያገኙ በመቶኛ	የመም/ት/ም/አመ/ልማት ዋና ስራ ሂደት	ከፍተኛ		በየወሩ	ሪፖርትና ግብረ መልስ	(ሀ/ለ)x100 ሀ=የትምህርት ሱፐርቪዥን አገልግሎት ያገኙ ለ=የታቀደየትምህርትሱፐርቪዥን አገልግሎት ብዛት	የመም/ት/ም/አመ/ልማት ዋና ስራ ሂደት
		የተሰሩ ጥናትና ምርምር ብዛት	የት/ጥናትና ምርምርፈተናና ምዘና ዋ/የስራሂደት	ከፍተኛ	በየአመቱ	ሪፖርት/የጥናት ሰነድ	ሀ	ሀ=የተሰሩ ጥናትና ምርምር ብዘት	የቢሮ ኃላፊዎች
	14 የምዘናና የሽልማት አሰራር ማሻሻል	የተመዘኑ በመቶኛ	የለውጥስራዎች/አ/አ/ክትትል ምዘና ንዑስ የስራ ሂደት	ከፍተኛ	በየአመቱ	የምዘና ሪፖርት	ሀ/ለx100	ሀ=የተመዘኑ ለ= አጠቃላይ መመዘን ያለባቸው	የቢሮ ኃላፊዎች
		በምዘና ተለይተው እውቅና እና ሽልማት የተሰጣቸው	የለውጥስራዎች/አ/አ/ክትትል ምዘና ንዑስ የስራ ሂደት	ከፍተኛ	በየአመቱ	የሽልማት ሪፖርት	ሀ	ሀ= እውቅና እና ሽልማት የተሰጣቸው	የቢሮ ኃላፊዎች

		የትምህርት እድል ያገኙና በውሳኔ ሰጭነት የተሳተፉ ሴቶች በመቶኛ						ሀ= የተፈራረሙ የትስስር ስምምነት ሰነድ ብዛት	
		የተፈራረሙ የትስስር ስምምነት ሰነድ ብዛት							
	16.የአመራሩን፣ የመምህሩንና የፈጻሚውን ብቃት ማሳደግ	የተሰጡ የስልጠና ዓይነቶች ብዛት	የመም/ት/አመ/ልማት ዋና ስራ ሂደት	ከፍተኛ	በሩብ አመት	የስልጠና ሪፖርት	ሀ	ሀ=ለአመራር፣ ለፈጻሚና ለመምህሩ የተሰጡ የስልጠና ዓይነቶች	የመም/ት/አመ/ልማት ዋና ስራ ሂደት
		የተፈጠሩ ሞዴል	የመም/ት/አመ/ልማት ዋና ስራ ሂደት	ከፍተኛ	በሩብ አመት	ሪፖርት	ሀ	ሀ= የተፈጠሩ ሞዴል	የለውጥስራዎች/አ/አ/ክትትል ምዘና ንዑስ የስራ
መማርና እድገት	17.የመምህራንና የት/አመራር የሙያ ብቃት ማረጋገጥ	የሙያ ብቃት ምዘና የተሰጣቸው መምህራንና የት/አመራር	የመም/ት/አሙያ ፍቃድና እድሳት ዋና የስራ ሂደት	ከፍተኛ	በየአመቱ	ሪፖርት	ሀ	ሀ= የሙያ ብቃት ምዘናና የተሰጣቸው መምህራንና የት/አመራር	የቢሮ ኃላፊዎች
		የሙያ ብቃት ምዘና ማረጋገጫ የተሰጣቸው መምህራንና የት/አመራር	የመም/ት/አሙያ ፍቃድና እድሳት ዋና የስራ ሂደት	ከፍተኛ	በየአመቱ	ሪፖርት	ሀ	ሀ= የሙያ ብቃት ምዘናና ማረጋገጫ የተሰጣቸው ምምህራንና የት/አመራር	
	18.የትምህርት ኢንፎርሜሽን ኮምንኬሽን ቴክኖሎጂ ካፒታል ማሳደግ	የፕላዝማ ትምህርት አገልግሎት ያገኙ የትምህርት ተቋማት በመቶኛ	የትምህርት ኢን/ኮሚኒኬሽን ዋና የስራሂደት	ከፍተኛ	በሩብ አመት	ሪፖርት	ሀ/ለ(100)	ሀ=የፕላዝማ ትምህርት አገልግሎት ያገኙ የት/ተቋማት ብዛት ለ=አጠቃላይ የፕላዝማ አገልግሎት ማግኘት የሚገባቸው ተቋማት ብዛት	የትምህርት ኢን/ኮሚኒኬሽን ዋና የስራሂደት

		የመደበኛ ትምህርት በራዲዮ አገልግሎት ያገኙ ትምህርት ተቋማት በመቶኛ					ሀ/ለ(100)	ሀ=የመደበኛ ት/በራዲዮ አገልግሎት ያገኙ የት/ተቋማት ብዛት ለ=አጠቃላይ ት/በራዲዮ አገልግሎት ማግኘት የሚገባቸው ተቋማት ብዛት	
		በFM 94.7 ጣቢያ የተላለፉ የትምህርት ንቅናቄ እና አጠቃላይ አድማጮች ፕሮግራም ብዛት					ሀ	ሀ=በFM 94.7 ጣቢያ የተላለፉ የት/ንቅናቄ እና አጠቃላይ አድማጮች ፕሮግራም ብዛት	
		በስኩል ኔት ወርክ ተገናኝተው አገልግሎት ማግኘት የቻሉ ት/ተቋማት መቶኛ					ሀ/ለ(100)	ሀ=በስኩል ኔት ወርክ ተገናኝተው አገልግሎት ማግኘት የቻሉ ት/ተቋማት ብዛት ለ=ስኩል ኔት ወርክ ማግኘት የሚጠበቅባቸው ተቋማት ብዛት	
		አፈጻጸማቸውን አውቶሜት ማድረግ የቻሉ የትምህርት ተቋማት በመቶኛ					ሀ/ለ(100)	ሀ=አፈጻጸማቸውን አውቶሜት ማድረግ የቻሉ የት/ተቋማት ብዛት ለ= አጠቃላይ የትምህርት ተቋማት ብዛት	

5.2 የመለኪያ አሁን ያለበት ደረጃ (Base line) እና ኢላማ (Target) በየአመቱ የሚተነተንበት መግለጫ

እይታ	ስትራቴጂያዊ ግቦች	መለኪያ		የመለኪያ መግለጫ	የስትራቴጂ ዘመኑ ኢላማ	ነባራዊ መነሻ	ኢላማ					ስትራቴጂያዊ እርመረጃዎች	ባጀት
							2008	2009	2010	2011	2012		
ተገልጋይ/ 40	1.የትምህርት ጥራት ማሻሻል	በ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና አማካይ ውጤት 50%ና በላይ ያመጡ ተማሪዎች በመቶኛ		ከተፈተኑት ተማሪዎች መካከል በ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና አማካይ ውጤት 50%ና በላይ ያመጡ ተማሪዎች	90	30.09	50	60	70	80	90	የትምህርት ቤት መሻሻል መርሀ ግብር /School improvement programme/ የአጠቃላይ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ማሻሻያ መርሀ ግብር /Curriculum Improvement Programme/	
		በ10ኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተና 2፡00 እና ከዚያ በላይ ያመጡ ተማሪዎች በመቶኛ		ከተፈተኑት ተማሪዎች መካከል በብሄራዊ ፈተና አማካይ ውጤት 2.0 እና በላይ ያመጡ ተማሪዎች	96	81.4	85	88	92	95	96		
		በ12ኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተና ውጤት 350 እና ከዚያ በላይ ያመጡ ተማሪዎች በመቶኛ		በ12ኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተና ውጤት 350 እና ከዚያ በላይ ያመጡ ተማሪዎች	70	40.16	50	55	60	65	70		
		በክፍል የፈተና ውጤት አማካይ 50% እና በላይ ያመጡ ተማሪዎች በመቶኛ	ከ1ኛ-8ኛ ክፍል	በክፍል የፈተና ውጤት አማካይ 50% እና በላይ ያመጡ ተማሪዎች	100	94.2	95	96.5	98	99	100		
			ከ9ኛ-11ኛ ክፍል		100	91.25	95	96.5	98	99	100		
